# ከፈተና በኋላ
# የጠላትን ደጅ መውረስ

ታውቃላችሁ... አንድ ትንሽ ሐሳብ አለችኝ፡ ማለት፡ የእግዚአብሔር ቃል በምናነብበት ጊዜ ሰዎች ሲቆሙ ማየት፡ እያሰብኩ ነበር። እናንተስ አትፈልጉም? ክብርን ለመስጠት እንደምንቆም፡ ስለ ለሀገራችን እንደምንቆም፡ ስለ ቃሉ ለምን አንቆምም አሁን?

2 እንደቆምን አንድ ደቂቃ ብቻ። ባለፉት ቅርብ ቀናት፡ አንዲት አንቀጽ አነብቤ ነበር፡ ትናንት ማታም ስለ ክርስቶስ ስለታመኑ ሰዎች እያሰላሰልኩ አመሸው። እናንተም እስካሁን ካልታመናችሁለት፡ ለምን ዛሬ አትታመኑለትም?

3 ከሰባ-አምስት ዓመታት በፊት፡ አንድ ታላቅ ወንጌላዊ ሰው ነበረ፡ ሰሙ ትዝ አይለኝም። አርተር ማኮይ ይመስለኛል፡ አገሪቱን በሙሉ ዞሯታል። አንድ ቀን ማታ በህልሙ ወደ ክብር ተወሰዶ አየና። መግቢያው በር ድረስ ደርሶ፡ አናስገባህም ተባልኩኝ ብሎ ይናገራል። እኔ “አርተር ማኮይ ከዩናይትድ እስቴትስ ነኝ። ወንጌላዊ ነኝ፡” አልኳቸው አለ።

4 ጠባቂው ግን፡ ወደ ውስጥ ሄደና፡ (ህልም ነው እንግዲህ)፡ ወደ ውስጥ ሄደና፡ “ጭራሽ ሰምህን አላገኘሁትም” አለው።

እርሱም “እንዴ፡ እኔ'ኮ ወንጌላዊ ነበርኩ፡” አለ።

“ጌታዬ፤ እኔ'ኮ... ” ይለዋል።

5 “እንዴ፡ የሆነ የተሳሳተ ነገር አለ... ሌላ አማራጭ ይኖር ይሆን፡” አለው።

6 “የለም፡ ጌታዬ። መጽሐፉ ከኔ ጋር ነው። ሰምህን ፈጽሜ ላገኘው አልቻልኩም፡” አለው።

እርሱም “ታዲያ፡ ሌላ ማድረግ የሚገባኝ ነገርስ አለ? ” አለው፤

7 “ጉዳይህ በነጭ ዙፋን ፍርድ ይግባኝ ማሰማት ትችላለህ፡” አለው። አምላክ ሆይ፡ ማረኝ። እኔ እዛ መሄድ አልፈልግም።

8 “እንግዲህ፡ ተስፋዬ ይህ ብቻ ከሆነ፡ ይግባኝ እላለሁ፡” አለ።

9 ከዛ በኋላ በጣም እሩቅ የተጓዝኩ ይመስለኛል አለ፡ እና... ጉዞ እንደጀመረ፡ ጨለማ ነበር ከዛ በኋላ እየበራ እየበራ ሄደ፡ ብርሃኑ የቆመበት ልዩ ስፍራ አልነበረውም፡ በትክክል ግን መኃሉ ላይ ነበርኩ አለ። እና “ወደ ፍርዴ ዙፋን የቀረበው ማነው? ” ብሎ ተናገረ፤

10 እርሱም “እኔ አርተር ማኮይ ነኝ። ወንጌላዊ ነኝ፡ ብዙ ነፍሳት ወደ መንግስት ልኬአለሁ፡” አለ።

እርሱም “ሰምህ በመጽሓፉ ላይ አልተገኘምን? ” አለው።

“አልተገኘም።”

“ስለዚህ ወደ ችሎቴ አቤቱታ አቅርበሃል? ” አለው።

“አዎን፡ ጌታዬ።”

11 “ፍርድህን ታገኛለህ። በሕጎቼ እፈርድብሃለሁ። አርተር ማኮይ፡ ውሸት ተናግረህ ታውቃለህ? ”

12 “በብርሃኑ ፊት እስክቆም ድረስ መልካም ሰው ነኝ ብየ አስብ ነበር፡” አለ። “በብርሃኑ ፊት ግን፡ ኃጢአተኛ ነበርኩ፡” ይላል። የሁላችንም እጣ ፈንታ ይህ ነው። አሁን ደህንነት ሊሰማችሁ ይችላል፡ ብቻ እዚያ እስክትመጡ ድረስ ጠብቁ። እዚህ ቅባት ሲሆንላችሁ ምን ስሜት ይሰማችኋል? ምንም ታናሽነት ቢሰማችሁ! ነጭ ዙፋን ፍርድ ፊት ምን ይጠቅማል?

“ውሸት ተናግረህ ታውቃለህ? ” አለው፤

13 እርሱም፡- “እውነተኛ ነኝ ብዬ ሳስብ ነበር፡ ትንንሽ ነጭ ውሸቶች ናቸው ብዬ ያሰብኳቸው አንዳንድ ትናንሽ ነገሮች፡ እዚያ ትልልቆች እና ጨለማ ሆኑብኝ” ይላል።

“አዎን፡ ጌታዬ፡ ዋሽቻለሁ።” አለ።

“ሰርቀህስ ታውቃለህ? ” አለው፤

14 “በዚህ ጉዳይ ታማኝ፡ ሰርቄ የማላውቅ ይመስለኝ ነበር፡” አለ። በዚያ ግን “በብርሃኑ ፊት ግን፡ የ—የሳትኳቸው አንዳንድ ጉዳዮች እንዳሉ ተገነዘብኩ፡ ያም ትክክል አልነበረም፡” አለ።

“አዎን፡ ጌታዬ፡ ሰርቄያለሁ፡” አለ።

“ፍርዴ... ” ይህ ነው አለው፡

15 ፍርዱን ለመስማት ተዘጋጀ፡ “ለዲያብሎስ እና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ሂድ አለው፡” ወድያው አጥንቶቼ ሁሉ መለያየት ጀምሩ።

16 “ከዛ በኋላ በሕይወቴ ከሰማኋቸው ድምጾች ሁሉ ይልቅ ጣፋጭ ድምፅ ሰማሁ፡” አለ። እንዲህ አለ፡- “ለማየት ዞር ብዬ፡ ከዚህ በፊት ካየኋቸው ሁሉ ይልቅ የሚያምር ፊት አየሁ፡ ከእናቴ ፊት ይልቅ የሚያምር እናቴ ከምትጠራኝም ይልቅ የሚጣፍጥ ድምፅ።” አለ፡- “ዙሪያውን አየሁ። ድምጽም ሰማሁ፡ ‘አባ፡ እውነት ነው፡ ውሸቶችን ተናግሯል፡ ታማኝም አልነበረም። ግን፡ በምድር ለኔ ቆሞልኛልና፡’ ‘አሁን በእርሱ ቦታ እኔ እቆምለታለሁ፡’ አለ።”

17 ለእኔም እንዲሆንልኝ የምፈልገውም ይህ ነው። አሁን ለእርሱ መቆም እፈልጋለሁ፤ ጊዜው ሲደርስ፡ በኔ ቦታ እሱ ይቆማል።

18 ከዘፍጥረት 22፡ 15ኛ፣ 16ኛ፣ 17ኛ፣ እና 18ኛ ቁጥሮችን እናንብብ።

**የእግዚአብሔር መልአክም አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው።**

**እንዲህም አለው፤ እግዚአብሔር። በራሴ ማልሁ ይላል፤ ይህን ነገር አድርገሃልና፡ አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና**

**በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ፡... ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና፡ በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ፤ ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል፤**

**የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፤ ድምጼን ሰምተሃልና።**

እንጸልይ።

19 የሰማይ አባት ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡ የተነበበው ወሰደህ አሁን፡ አገልግለን። ጌታ ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ወሰዶ፡ ለእያንዳንዱ ልብ ያድርስ። ዛሬ ከሰዓት መሻቶቻችን ብዙ ናቸውና፡ ጌታ ሆይ፡ ይሳኩልን። ደስታችንም ሙሉ ይሆን ዘንድ፡ አብዝታችሁ ጠይቁ ብለኸናል። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

አረፍ አረፍ በሉ።

20 ይህን ጽሑፍ፡ ርዕስ ልሰጠው። ማይክሮፎኑ አጠገብ መቆም ያለብኝ፡ ድምጼ ስለደከመ ነው። ዋጋ የሚያስከፍል ነገር እንዳለ አውቃለሁ፣ በጥቂቱ ግን እንታገሳለን። **ከፈተና በኋላ የጠላትን ደጅ መውረስ፡** ብየ እጠራዋለሁ።

21 መድረካችን ከአብርሃም በጣም አስደናቂ ትዕይንቶች መካከል በአንዱ እንጀምረዋለን። አብርሃም የአማኞች አባት መሆኑን ታውቃላችሁ። የተሰፋው ቃል የተገባለት ለአብራሃም ነበር። በክርስቶስ በኩል፡ ከእርሱ ጋር ወራሾች ሆነን፡ የተሰፋውን ቃል የምንካፈልበት ብቸኛ መንገድ፡ በአብርሃም በኩል ነው። አብርሃም፡ ተራ ሰው ነበረ፡ በእግዚአብሔር ስለተጠራ ግን ለጥሪው ታማኝ ሰው ነበረ። እግዚአብሔር ሲያናግረው፡ አብራሃም አንድም ቀን ድምጹን ተጠራጥሮት አያውቅም። ታምኖ ጠበቀ። ምንም ያህል አስቸጋሪው ቢሆን እንኳን፡ ታምኖ ጠበቀ።

22 ስለዚህም ወንድ ልጅ ቃል ተገባለት። ተሰፋውን የሚቃወም የትኛውን ነገር እንዳላየ በመቁጠር፡ ልጁን ለመቀበል ሃያ-አምስት ዓመት ጠበቀ። ይህም፡ የምድር ቤተ ሰዎች ሁሉ፡ በዚህ ልጅ በኩል፡ እንዲባረኩ ነው። ፓትርያርኩም ለጥሪው እና ለተሰፋው ቃል ታማኝ ሆነ።

23 እኛ መሆን ለሚገባን ነገር ሁሉ ምሳሌ ሆነ። አሁን እኛ፡ በክርስቶስ የሞትን ስንሆን፡ የአብርሃም ዘር ነን።

24 እንግዲህ አብራሃም፡ ሁለት ዘር ነበሩት። አንደኛው የተፈጥሮ ዘር ሲሆን፡ ሌላኛው ደግሞ መንፈሳዊ ዘር ነበር። አንደኛው በሰጋው በኩል፡ ተፈሮአዊ ሲሆን፡ ሌላኛው ደግሞ የእምነቱ ዘር ነበር፡ በተሰፋው ቃል የአብርሃም ዘር የምንሆንባት፡ እምነት።

25 እና ለሃያ-አምስት፡ ረዥም ዓመታት ከተፈተነ በኋላ፡ ደካማ ከመሆን ይልቅ፡ እየበረታ ሄደ። እስተውሉ፡ በመጀመሪያው ዓመት ባይሳካ፡ በሚቀጥለው ዓመት የበለጠ ተዓምር ይሆናል፡ ገና ሁለተኛው አመቱ ነውና። ዕድሜው እየሸመገለ፡ አካሉም እየደከመ፡ እነዚያን ዓመታት አስቆጠረ። ማህፀኖቿም፡ የሳራ ማህጸን፡ ባለበት (ሁኔታ) መኻን ነው። ጉልበቱ ሁሉ አልቋል፡ ሙሉ በሙሉ... የማይቻል ሆኗል።

26 ያኔ እግዚአብሄር ያደረገውን አስባችሁት ታውቃላችሁ? እያችሁ፡ ማህጸኗ መውለድ የሚችል ብቻ አይደለም ያደረገው። አስታውሱ፡ ምክንያቱ፡ ይህን ካደረገ፡ አስታውሱ እንደዛው ካደረገ... በዚያ ዘመን፡ ለህፃኑ የላም ወተት ለመስጠት፡ ጤና የሚጠብቁባቸው፡ ንጹህ ጡጦዎች አልነበራቸውም። እያችሁ? በተጨማሪ... ወተት የሚያመነጩ ስሮችዋ ደርቋል። ስለዚህ

እንደዚያ—ሊያደርግ አይችልም... ይልቅ ግን ሌላ የተፈጸመ ክስተት መኖሩ ግድ ነው።

27 የመቶ ዓመት አሮጊት ሴት፡ ምጥ ስታምጥ፡ አሰቧት እስኪ። ልቧ ሊቋቋመው አይችልም። ለአርባ ዓመት ሴት እንኳን ይህን ለማድረግ ይከብዳል። ልቧ ሊቋቋመው አይችልም ነበር። ምን እንዳደረገ ግን አውቃችኋል? ካስተዋላችሁ...

28 ብዙዎቻችሁ ላትስማሙ እንደምትችሉ አውቃለሁ። ምናልባት ይሄን ለመናገር ብቻ ቢሆን? እንደው፡ የ... የግል ሐሳቤ ብቻ ይሆን ነበር።

29 እያችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ መጽሐፍ ነው። ከትምህርት ቤቶች እና፡ ከቲኦሎጂ ምሁራን እንዲሰወር ተደርጎ የተፃፈ ነው። ኢየሱስም እግዚአብሔርን አመሰገነ። ሰንቶች ታውቃላችሁ? እንዲህ አለ፦ "አባት ሆይ፡ ይህን ከጥበበኞች እና ከአስተዋዮች ሰውረህ፡ መማር ለሚወዱ ለሕፃናት ገልጠኸዋልና አመሰግንሃለሁ።" የፍቅር መጽሐፍ ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ወደ ልባችሁ ሲመጣ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ትፋቀራላችሁ፡ መጽሐፍ ሲናገር፡ እራሱንም ይገልጽላችኋል ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን፡ በመስመሮች ውስጥ ለውስጥ የተጻፈ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ የሚባለው፡ እግዚአብሔር የተሰፋ ቃሎቹ እራሱ ሲተረጉማቸው ነው።

30 ለምሳሌ፡ ልክ እንደ ሚስቴ፡ ኦህ፡ ከሌላው ዓለም ሁሉ ይልቅ ድንቅ ሴት ናት፡ በጣም እወዳታለሁ። ትወደኛለች። ከቤት ስርቅ፡ ደብዳቤ ትጽፍልኛለች፡ "ቢሊዬ፡ ዛሬ ልጆቹን አስተኛቻቸዋለሁ። ገላዬን ተታጥቤአለሁ፡" ያደረገችውን ሁሉ በዝርዝር፡ ትነግረኛለች። በርግጥ ደብዳቤው ውስጥ የተናገረችው ይህ ነው። ነገር ግን፡ እያችሁ፡ በመስመሮቹ ውስጥ ለውስጥ ማንበብ እስክችል—ድረስ፡ እጅግ አንድ ነን፡ በጣም እወዳታለሁ። ምን ለማለት እንደፈለገች አውቄአለሁ፡ እያችሁ፡ ባትነገረኝ ገብቶኛል፡ እያችሁ። ምን ለማለት እንደፈለገች—አውቃለሁ፡ ለሷ ያለኝ ፍቅር፡ እና መረዳት ይህ ነውና።

31 መልካም፡ መጽሐፍ ቅዱስም በዚህ መንገድ ነው የተጻፈው። እያችሁ? ተምረናል የሚሉ—ላይ ላዩን ይዞሩታል እንጂ፤ ፈጽመው አይደርሱበትም። እያችሁ፡ "እሱን ለማወቅ" ከቃሉ ጋር፡ ከእሱ ጋር፡ በፍቅር መኖር አለባችሁ። እያችሁ?

32 እዚህ ጋር፡ ያደረገውን ተመልከቱ። መጽሓፍ ቅዱስ፡ አብራሃምና ሳራ ሁለቱም፡ "እጅግ-ያረጁ፡" ነበሩ ይላል። ብዙ ዘመን በዚያ የኖሩ ሰዎች ስለሆኑ አይደለም። መጽሃፍ ቅዱስ፡ "በዕድሜ እጅግ-ያረጁ ነበሩ" ይላል።

33 አሁን ተከታተሉ፡ ሰንናገርለት የነበረ መልአክ፡ ኤሎሂም፡ ራሱ እግዚአብሔር፡ ከተገለጠ በኋላ። አብራሃምን፡ "የዛሬ አመት እጎበኝሃለሁ፡" ብሎ ተናገረው። አሁን ከላይ ጀምራችሁ ተመልከቱት፡ በዚህ ሁሉ ጉዞ ውስጥ፡ የቤተ ክርስትያን ጥላ ነበሩ።

34 አሁን ተመልከቱ። የተፈጸመው ይህ ነው። ከመሬት ተነስቶ፡ ሳራን አልጎበኛትም፡ አብራሃምን አልጎበኘም። ነገር ግን ወደ ወጣት ወንድ እና ሴት መለሳቸው። አሁን እንግዳ ነገር ሊመስል ይችላል፡ ነገር ግን ሌላው ቃላት መርምሩና፡ አንድ ላይ ጥመሩት። ቃል ሁሌም የበራ ነውና፡ እናንተም ከቃሉ

ጋር መብራት አለባችሁ። አሁን፡ አስታውሱ፡ ልክ ከዚያ በኋላ፡ ልክ መልአኩ እንደተገለጸላቸው ወድያውኑ...

35 እንደው ይታየኛል፡ የሳራ ሽበት፡ ትከሻዋ ላይ ሻርፕ ጣል ያደረገች የነተበች ትንሽ የአቧራ መከላከያ ቆብ ያላት፡ ምስኪን አሮጊት፡ ከዘራ ይዛ፡ ወድያ ወዲህ ትላለች። "እኔ፡ ከጌታዬ ጋር እተኛለሁን፡ እርሱም'ኮ፡ ሸምግሏል? " አያችሁ? አብራሃምም፡ ከዘራ ይዞ፡ ባለ ረዥም ጺም፡ በእድሜ እጅግ-ያረጀ፡ ነበር።

36 ይታየኛል፡ በነጋታው፡ ትከሻው ቀና ማለት ጀምሯል፡ ሻኛውም ከጀርባው ሸሽቷል። ጸጉሯም ታድሷል። ወደ ወጣት ሴት እና ወንድ ተመለሱ። ይህም ከአብራሃም ንጉሳዊ ዘር ጋር ወደፊት ሊያደርግ ያለውን ያሳያል፡ አያችሁ፤ ይህም "በቅጽበት ዓይን፡ በድንገት መቀየራችን፡ እና በአንድነት መነጠቃችን፡" ነው።

37 የሆነውን ተመልከቱ። አሁን ይህንን ላረጋግጥላችሁ። ከነበሩበት ሰፍራ ከጎሞራ፡ ጀምረው ተጉዘው፡ እስከ ፍልስጤም ምድር፡ እስከ ጌራር ድረስ ሄዱ። አስተውላችኋል? ምን ያህል እንደሚርቅ፡ ካርታው ላይ እዩት። በዛ እድሜ ላሉ ባለ ትዳሮች እጅግ ሩቅ ጉዞ ነው።

38 ከዚያም፡ በተጨማሪ፡ በ—በፍልስጤም ምድር ላይ፡ አበሜሌክ የተባለ ወጣት ንጉስ ነበረ፡ ሚስትም ይፈልግ ነበር። ብዛት ያላቸው ፍልስጤማውያን ቆንጆ ሴቶች ነበሩት፡ እሱ ግን አሮጊቷን ሲያያት፡ "እጅግ ታምራለች፡" አለ፡ በፍቅሯ ወደቆ ሊያገባት ወደደ። እውነት ነው። ኧሀ-ህ። አያችሁ፡ ዉብ ነበረች። አያችሁ?

39 ወደ ወጣት ሴት ተመልሳለች። አስተውሉ፡ ልጅ ለመውለድ፡ ወጣት መሆኗ ግድ ነበር። እግዚአብሔር አዲስ ፍጥረት አደረጋት። ልጁን ለማሳደግ፡ ወጣት መሆኗ ግድ ነበር። አብራሃምን፡ አስታውሱት፦ "አካሉ ፈጽሞ የሞተ አካል ነበር፡" ሳራ ስትሞት አብራሃም... ይመስለኛል፡ ይስሓቅ አርባ-አምስት አመት ሲሆን፡ ሳራ ሞተች። አብራሃምም ሌላ ሚስት አገባ፡ ከዛ በኋላ ከሴቶች ልጆች ውጪ ሰባት ወንድ ልጆች ወለደ። አሜን።

40 አያችሁ፡ በመስመሮቹ ውስጥ ለውስጥ አንብቡ። ጥላ ነው። በአብራሃም ልጆች ሁሉ ላይ ምን ሊያደርግ እንዳለ ያሳያልና። ወዳጆች ሆይ፡ የደከመው ትከሻችን እና ሌላ ነገራችን ምንም ልዩነት አይፈጥርም፡ አሁን ተቃርበናልና። አሁን ሽበታችን ቢሆን ሌላ ነገራችን፡ ምንም ችግር የለውም። ወደ ኋላ አናይም። ወደ ግባችን ወደ ፊት ብቻ እንመልከት።

41 አስታውሱ፡ አሁን ያየነው ምልክት፡ የተሰፋው ቃል ልጅ ከመምጣቱ በፊት፡ አብራሃምና ሳራ ያዩት የመጨረሻው ምልክት ነው። ሰዓቲቱ ላይ እንደደረስን እናምናለን።

42 ፓትሪያሪኩም፡ ልጁ ከተወለደ በኋላ... የአስራ ሁለት ዓመት፡ ደስ የሚል ታዳጊ፡ ባለ ከርል-ጸጉር ልጅ፡ ቡናማ ዓይን ያለው፡ ይስሓቅን አሰባችሁታል? እናቱም፡ ወጣት ቆንጆ ሴት፡ ምን ተሰምቷት ይሆን ብዬ አሰባለሁ፡ አባቱም። ነገ የሚፈጠረውን፡ ፈጽመን አናውቅምና፤ አሁን፡ ለምሳሌ ያህል፡ አንድ ቀንም፡ እግዚአብሔር እንዲህ አለው። "በዚህ ልጅ በኩል፡ የአሕዛብ ሁሉ አባት አድርጌህአለሁ፡ ይሁን እንጂ ይህን ልጅ እኔ ወደማሳይህ ረጅም ተራራ ውሰደውና፡ መሰዋዕት አድርገው፡ እንድትገድለው እፈልጋለሁ።" ይህን ማመን ትችላላችሁ?

43 አሁን እንዲህ አይነቱ ፈተና ውስጥ ግቡ ተብላችሁ አታውቁም። በዚህ ጊዜ እንዲህ አያደርግም። ምሳሌዎች፡ እና ጥላዎች ናቸው።

44 አብራሃም ፈራ′ዴ? ኖ፡ ሰር። አብራሃም ግን እንዲህ አለ፦ “እኔ ራሴ እንደ ሙት በነበርኩ ጊዜ እሱን ወልጃለሁና፡ ከሞት ሊያስነሳው እንደሚችል በሙላት አምኛለሁ። የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ይህን አድርግ ብሎኝ፡ ለትዕዛዙ ታማኝ ሆኜ በመጽናቴ፡ ዋጋዬ እንደከፈለኝ፡ በወንድ ልጅ እንደ ባረከኝ ሁሉ፤ እኔ ራሴ እንደ ጥላ፡ ከሙታን መካከል ተቀብየዋለሁና፡ አሁንም እግዚአብሔር ከሙታን ሊያስነሳው ይችላል።”

45 ኦ፡ ማይ፡ ወዳጆች ሆይ! እናንተ ጴንጤዎች፡ በልሳን ትናገሩ ዘንድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ከሰጣችሁ፡ በጎነቱም ምሕረቱም እንዲሁም የፈውሱን ኃይል፡ ምን ያህል ልታምኑት በተገባ! በአገሪቱ ያሉ የሰነ መለኮት ምሁራን ለማሳፈር፡ ይህን አደረገ! እነርሱ ይህ ሊሆን አይችልም ይላሉ፡ እግዚአብሔር ግን ሰለ ገባው ኪዳን ያደርጋል። ሰለዚህ ከትጥቃችሁ ጋር፡ ከቃሉ ጋር፣ ከሰይፋችሁ ጋር ጽኑ፡ የጌታን ቃል እመኑት። ጌታ ከተናገረ፡ ሆነ ነው!

46 አስተውሉ፡ አሁን፡ ከበቅሎዎቹ ጋር፡ ከሰፍራው የሶስት-ቀናት ጉዞ ፈጅቶበታል። ድሮ አሳሽ ጥበቃ ሆኜ በምሰራ ጊዜ፡ ጉዞ እችላለሁ፡ በበረሃው፡ በየቀኑ ሰላሳ ማይልስ ያህል እጓዛለሁ፣ ይሄን ሰል ግን፡ ባለ ነዳጅ እግር ይዞን ነው። ሰዎቹ ግን፡ ብቸኛው ማጓጓዣቸው፡ እህያ መንዳት——ወይም መጓዝ ነው። ሰለዚህ ከቤቱ የሶስት-ቀናት ጉዞ አደረገ፤ ከዛ በኋላ በበረሃ፡ አይኑን አነሳና፡ ተራራውን ከርቀት ተመለከተ።

47 ይሰሐቅን ወሰዶ እጆቹን አሰረ። ዘፍጥረት 22 ላይ፡ ሁላችንም እናውቀዋለን፡ ያ ማለት፡ የክርስቶሰ ጥላ ነበር። ኢየሱሰ ታሰሮ፡ ወደ ተራራው፡ ቀራንዮ ተራራ እንደተነዳ፡ ወደ ተራራው መራው፤ አዎን፡ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን የሰጠበት ጥላ ነበር።

48 በደረሱ ጊዜ ግን፡ ታዛዥ ነበርና፡ ይሰሐቅ የመጠራጠር አዝማምያ ጀመረ። “አባዬ፡ እንጨቱም ይኸው፡ መሰውያውም ይኸው፡ እሳቱም ይኸው፡ መሰዋዕቱ የት አለ? ” አለው፤

49 አብራሃምም፡ የእግዚአብሔር ቃል በሰፍራው እንዳለ፡ በልቡ እያወቀ፡ እንዲህ አለ፦ “ልጄ ሆይ፡ እግዚአብሔር ለራሱ መሰዋዕትን ማዘጋጀት ይችላል አለው።” ሰለዚህ ቦታውን “ያሕዌ-ይሬ።” ብሎ ጠራው።

50 ልጁን ባሰረ ጊዜም፡ ልጁ ለሞት የታዘዘ ነበር፣ በመሰውያው ላይ አስተኝቶ፡ ቢላውንም ከሰገባው መዘዘ፡ የገዛ ልጁ ህይወት መግደል ጀመረ። ይህ ሲያደርግ ግን፡ አንድ ነገር እጁን ያዝ አደረገውና፦ “አብራሃም ሆይ፡ እጅህን መልሰ።” በማለት፡ ተናገረው።

51 እናም በዚያን ጊዜ፡ ቀንዶቹ በምድረ በዳ ቊጥቋጦ የተያዘ፡ አንድ አውራ በግ፡ ከበሰተጀርባው አሰተጋባ።

52 በጉ ከየት መጣ፡ ብላችሁ አሰባችሁ ታውቃላችሁ? አስታውሱ፡ ምድሪቱ በአንበሶች እና በተኩላዎች በቀበሮዎችም፡ በግ-በሚውጡ አውሬዎች ተሞልታለች። በተጨማሪ ምን ያህል ከሰልጣኔ የራቀ ሰው ነበር? ደግሞም፡

ውሃ በሌለበት፥ በተራራ ጫፍ ላይ ነው። መሰውያን ለመሰራትም፥ ከዙርያው፥ ድንጋዮችን መልቀም አለበት። ታድያ በጉ ከወዴት መጣ? አያችሁ?

53 ራእይ ግን አይደለም። ደም ያለው፥ በግ ገድሏል። ምን ብሎ ነበር? “እግዚአብሔር ለራሱ መሰዋዕት ማዘጋጀት ይችላል።”

54 **እናንተስ** ከወንበሩ የምትነሱት እንዴት ነው? ሽባ የሆነ **ያንን** ልጅ፥ ወይም ወንበር ላይ **ያለኸው፥ አንተም** ከዛ፥ **አንቺ** የልብ ህመምተኛ የምትፈወሱት እንዴት ነው? ችግሩ ምንም ቢሆን፦ “እግዚአብሔር ራሱ ማዘጋጀት ይችላል።”

55 አብራሃም አመነ። ፓትሪያሪኩም ለተሰፋው ቃል ታማኝ ሆኖ ጠበቀ። እርሱም፥ የተሰፋ ቃል ገባለት፦ “ጫናው ምንም ቢበዛብህ፥ ቃሌን አምነሃልና፥ ዘርህ! ዘርህ የጠላቱን ደጅ ይወርሳል።”

56 ለምን? በአብራሃም ላይ፥ እንደ ምሳሌ፥ የተነሳበት ጠላት ሁሉ፥ አብራሃም-... ጠላቶቹ ሁሉ፥ “እሷ አርጅታለች። እኔ እጅግ ሽምግያለሁ። **ይህ** ሁሉ፥ እና ሌሎችም።” እያሉ ለተሰፋው ቃል የታመነ ሆነ።

57 አሁንም፥ ይህ ዓይነት እምነት ያለው ሰው፥ ጫናው ምንም ቢበዛበትም የጌታን ቃል ይታመናል። አሁን፥ ይህ ማድረግ ካቃታችሁ፥ የአብራሃም ልጆች አይደላችሁም። በአብራሃም ዘንድ የነበረች እምነት፥ ዘሩ ይህች ናት።

58 የአብራሃም ተሰፋ፥ “ዘሩ፥” ደግሞም፥ ቀደም ብየ እንደነገርኳችሁ፥ ንጉሳዊው ዘር ነው። ለአብራሃም የተሰጠው ይህ ማሕተምም፥ የተሰፋው ቃል ማሕተም ነው። እንደ ኤፌሶን 4:30 አገላለጽ፥ ንጉሳዊ ዘር፥ ፈተናን በጽናት ካለፉት በኋላ “በመንፈስ ቅዱስ የታተሙት፥” ናቸው። እስኪ አስቡት።

59 ብዙዎች መንፈስ ቅዱስን ተሞልቻለሁ። መንፈስ ቅዱስ አለኝ ብለው ያስባሉ። ብዙ ማረጋገጫዎች እና ምልክቶች ማሳየት ይችላሉ። ሆኖም፥ ግን፥ ከዚህ ቃል ጋር ካልተሰማማ፥ መንፈስ ቅዱስ አይደለም። አያችሁ?

60 ቃሉን በሙላት እመኑት፥ ከዛ ከፈተናው በኋላ ትታተማላችሁ። በቃሉ ውስጥ ባሉት ተሰፋ ቃሎች ሁሉ ስንታመን፥ የተሰፋውን ቃል ለማረጋገጥ፥ በመንፈስ ቅዱስ እንታተማለን። ይሄ ነው፥ አብራሃምም፥ በዚህ መልኩ ነው ያደረገው። የጠላታችን ደጅ መውረስ መብት የሚኖረን፥ ያኔና፥ ያኔ ብቻ ነው። አስቀድማችሁ ያንን ዘር ሳትሆኑ አይሳካላችሁም። አስታውሱ፥ በመጽሓፍ ቅዱስ...

61 በቀደም፥ በሂውስተን ወይም ሌላ ቦታ፥ በዚህ ጉዳይ ላይ... ሰብኬአለሁ፥ በዳላስ። ስለ **ምልክቱ።**

62 አያችሁ፥ እስራኤል ውስጥ፥ አንድ—አይሁዳዊ ሰው፥ በመገረዙ አይሁዳዊ እንደሆነ ሊያሳይ ይችላል። እግዚአብሔር ያለው ግን፦ “ደሙን ባየሁ ጊዜ! ደሙ ምልክት ይሆንላችኋል።”

63 እንግዲህ፥ የእንሰሳው ህይወት፥ ሊመጣ ላለው እውነተኛ ህይወት ምሳሌ ብቻ ነበረ እንጂ፥ በእንሰሳው ደም ውስጥ የነበረ ህይወት፥ መሰዋዕት ወደሚያቀርበው ሰው መምጣት አይችልም። ስለዚህ፥ ሂደቱ፥ ደሙ ራሱ፥ በበሩ እና በበሩ መቃን ላይ መቅላት ይኖርበታል።

64 ይሄን ለማድረግ፥ የተለየ እምነት እንደማያስፈልግ ለማሳየት፥ ሂሶጵ በሚባል ተራ ቅጠል ይረጫል። ወደ ቤተክርስትያን ለመምጣት መኪናህን ማስነሳት

እንዳለብህ፡ ያለውን ተራ እምነት፡ ብቻ ይኑርህ። አያችሁ? ብዙ ሰዎች ልዩ ነገር መሆን እንደሚገባቸው ያስባሉ... ግን፡ አይደለም፡ አይደለም፡ ስሕተት ነው። ደሙን ለመርጨት የሚያስፈልግህ ተራው እምነት ነው። ቃሉን ስማ፡ ቃሉን እመነው፤ እርጨው፡ ይሄው ነው። በፍልስጤም ከሚገኙ የሂሶጵ አረሞች፡ አንዱን አንሳና፡ በግንብ ስንጣቂዎችና፡ በየመንገዱ በቅሎ በሚገኝ አረም፡ ደማቸው ውስጥ ይነክሩትና መቃኖች እና ጉበኑ ላይ ይቀባል።

65 እና፡ አስታውሱ፡ ምንም ያህል ኪዳን ቢኖራቸውም፡ አንድ አይሁዳዊ የተገረዘ መሆኑን ለማሳየት ምንም ቢሞክር፡ ምንም ያህል ጥሩ ሰውም ይሁን አይገደኝም፤ ምልክቱ ካልያዘ በቀር—ኪዳኑ ሁሉ ፈራሽ ነው። “ደሙን ባየሁ ጊዜ፡” ብቻ ነውና።

66 አሁን፡ ደሙ፡ ወይም ምልክቱ ያለው፡ በቀመሩ ላይ፡ ወይም በክርስቶስ ደም ቀመር ውስጥ አይደለም፡ ምክንያቱ ደሙ የፈሰሰው ከሺዎች ዓመታት በፊት ነውና።

67 ግን፡ አያችሁ፡ ያንን... ቀመር ቢኖር ኖሮም፡ የእንስሳው ህይወት በሰው ላይ ሊመጣ አይቻለውም፤ ምክንያቱም የእንስሳው ህይወት ነፍስ የለውም። እንስሶች መልካምን ከክፉ ለይተው አያውቁምና። ነፍስ ያለው የሰው ልጅ ነው።

68 በድንግልና-የተወለደው፡ የእግዚአብሄር ልጅ፡ ኢየሱስ፡ ደሙን ባፈሰሰ ጊዜ ግን፡ በደሙ ውስጥ የነበረ ህይወት፡ ራሱ እግዚአብሔር ነው። መጽሓፍ ቅዱስ “በገዛ ደሙ፡ በእግዚአብሔር ሕይወት ድናችኋል፡” ይለናል። በእግዚአብሔር ህይወት እንጂ፡ በአንድ አይሁዳዊ፡ ወይም በአህዛብ ደም አልዳንንም። እግዚአብሔር፡ በድንግል የተወለደውን የደም ሕዋስ ፈጠረ። እሷ አንድም ወንድ አታውቅም... እንቁላሉም ከእሷ አልተገኘም።

69 ብዙዎቻችሁ እንቁላሉ የሷ ነው ብላችሁ ማመን እንደምትፈልጉ አውቃለሁ። ከሰሜት ውጪ እንቁላል የማይወርድ ከሆነ፤ ታድያ እግዚአብሔር ምን አደረገ? አያችሁ?

70 እንቁላሉ እና የደም ሕዋሱ ሁለቱንም ራሱ ፈጠራቸው፡ ያም ቅዱስ የእግዚአብሔር ማደርያ፡ ሆነ። “ቅዱሴን መበስበስን ያይ ዘንድ አልተወውም።” “ነፍሱን በሲኦል አልተዋትም።” ኦ፤ ማይ! ስጋው ቅዱስ ነበረ! እንቁላሉ ከየት እንደመጣ አያችሁ? ይሄን አታምኑም፡ ይሄን ካላመናችሁ’ማ፡ እንዴት ክርስትያን ነን ትላላችሁ?

71 “የዳንነው በእግዚአብሔር ደም ነው።” የእምነቴ አድራሻም ይህ ነው። በነብይ ደም አልተመላለስንም፡ በተራ ሰው ደም፡ ወይም የአስተማሪ፡ ወይም በቲኦሎጂያን ደም፡ አንኖርም። የምንኖረው በእግዚአብሔር ደም ነው። እግዚአብሔርም ተናግሯልና። ሰው ሆነ። ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ። ድንኳኑን፡ ከእኛ ጋር፡ እዚህ ዘረጋ፡ መገኛውን ቀየረ። እርሱ ዋርሳችን ነው። እንደ ሕጉም፡ ዘመድ ወዳጅ ሆነን። እግዚአብሔር በመካከላችንም አድሮ ሰው ሆነ።

72 ይህን አስቡት፡ ይህን ሲያደርግ፡ ከእርሱ ዘንድ የወጣው፡ መንፈስ፡ አምላክ ነበር፤ ያን መንፈስም በአማኞች ዘንድ ወረደ። ስለዚህ፡ በመሰዋዕታችን ዘንድ ባለው ህይወት፡ በዚያው ሕይወት ከሱ ጋር እንቆጠራለን።

73 ታዲያ ከመሰዋዕታችን ጋር የምንቆጠረው በዚህ ከሆነ፡ የእግዚአብሔር ህይወት በህዝቡ መካከል ሲመላለስ አይተው፡ እንዴት ንጹህ ያልሆነ ነገር ነው ይሉታል? "በእኔ የሚያምን ሁሉ፡ እኔ የማደርገውን ስራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል።" እጆቻችን ስንጭንበት-... ለገዛ ሓሳቦቻችን መሞታችን ስንቆጥር፡ ሕይወቱ ከመሰዋዕቱ ዘንድ ተመልሶ ይሄዳል። የሐይማኖት ተቋማት ወደ ስርዓታቸው እና ኮተታቸው እንዲገፋን እየፈቀድን፡ አምናለሁ እንዴት እንላለን? እኛ ሰለ እነኚህ ነገሮች ሞተናል።

74 ጳውሎስ፡ ፍጹም ለሆነው፡ ለክርስቶስ እስረኛ ስለነበረ "ማንም አያድክመኝ፡" አለ። እያንዳንዱ እውነተኛ ሰኬት ፍጹም ከሆነው ጋር የተሳሰረ ነው፡ ለእኔም ፍጹሜ ቃሉ ነው። በእውነት ከ—ከመንፈስ ለተወለዱ ሁሉም፡ እንዲህ ነው፡ ፍጹማቸው የእግዚአብሔር ቃል ነው። በሱ ዘንድ ታስሬአለሁ። እጆቼን በእርሱ ዘንድ ጭኜ። እርሱም ሰፍራየን ወሰዶልኝ፡ እራሴን በእርሱ ዘንድ ተቆጥሬአለሁ። እሱም እራሱ ከእኛ ጋር ለመቆጠር ቃል እንደገባ እናውቃለን። ይህም እውነተኛውን እምነት ያመጣል፡ የገዛ እምነታችሁ ሳይሆን፡ እናንተ የማትቆጣጠሩት፡ የራሱ እምነት። አስተውሉ አሁን። ተሰፋዉን... ያኔ ለእናንተ ቃል ሲገባላችሁ፡ ጊዜ፡ ያደርጋል። ራሱ ያደርገዋል።

75 ምንም ያህል ቸርቻች ውሰጥ ብትሳተፉ፡ የቱንም ዓይነት ጥምቀት፡ በሆዳችሁ በኩል፡ በጀርባችሁ በኩል፡ የቱንም ተጠመቁ። ማሕተሙ እስክያርፍባችሁ ድረስ፡ ከመሰዋዕቴ ጋር ተገናኝቼአለሁ የማለት መብት አይኖራችሁም።

76 የእግዚአብሔር ማሕተም ምንድነው? ኤፌሶን 4:30፡ እንዲህ ይላል፡ "እስከ ቤዛነት ቀን ድረስ የታተማችሁበትን፡ ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።" ከአንደኛው እስከ ሌላኛው ሪቫይቫል ድረስ አይደለም፡ በቤዛነት እስክትዋጁ ድረስ ዘለአለማዊ ማህተም ነው።

77 እንዲሁም፡ አስታውሱ፡ በእግዚአብሄር ሐሳብ ያልነበራችሁ ከሆናችሁ፡ ፈጽማችሁ ከእግዚአብሄር ጋር አትሆኑም። ቤዛ እንደሆነ ሰንቶች ታውቃላችሁ? እንግዲህ፡ ቤዛነትን ያገኘ ሁሉ ከመውደቁ በፊት ወደነበረበት መመለስ አለበት። እንዴት ነው፡ ያኔ ቤዛነት የማይገባን የነበርን፡ ሰለዚህ ሊቤዠን ከመጣ፡ ሁላችንም፡ "በሐጢአት የተወለድን፡ በዓመጽ የተጸነሰን፡ ሐሰትን እየተናግርን ወደ ዓለም የመጣን ነበርን"? ይህ የሚያሳየው እውነተኛው ክርስትያን የእግዚአብሄር የሐሳቡ መገለጫ መሆኑን ነው፡ ዓለም፣ ወይም ከዋክብት፣ አየር ወይም ሌላ ነገር ከመኖሩ በፊት። ዘላለማዊ ነበረ፡ እኛን መልሶ ሊቤዥን መጣ። በቃል የተነገረው፡ ከተገለጠ በኋላም-... ዳግም ሐሳብ ወደ መሆን የተመለሰው፡ እርሱ የእግዚአብሄር ሐሳብ ነው።

78 የቤዛነት ዋርሳችን! እግዚአብሄር መቤዠት ይችል ዘንድ፡ ከእኛ እንደ አንዱ መሆን ያስፈለገበት ምክንያት ይሄው ነው። ሌላው ማንም አይችልም። መልአክ ማድረግ አይቻለውም፡ ሌሎቹም አይችሉም። እኛን ለመቤዠት፡ እኛ እንደተፈተንን እሱም ይፈተን ዘንድ መውረድ ነበረበት።

79 አሁን ደግሞ ፍጥረታዊው የአብራሃም ዘር የሆነውን እንመልከተው። ፍጥረታዊ ዘር የነበሩትን ጥቂቶች እንመርምር፡ እና እግዚአብሔር ፍጥረታዊ ከሆነ ዘር ጋር ቃሉን የሚጠብቅ ከሆነ እንይ፡ እርሱም ይሰሐቅ ነው።

የእግዚአብሔርን ሙሉ ተስፋ ያመኑ እና ያልተጠራጠሩትን የተወሰኑ ፍጥረታዊ ዘር እንፈትሽ። በአስር ሺዎች ጊዜ ሺዎች ሲባዛ በሺዎች በሚቆጠር ተባዝተው እንደነበር፡ አሁን አስታውሱ፡ የተገረዘ እና ሌላው ሁሉ፡ የአብርሃም ዘር አልነበረም። አዎን፡ "ከውስጥ አይሁዳዊ የሆነ እንጂ፡ በውጭ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለም።" ከእነሱም፡ ብዙዎች፡ መራራ ውድቀት፡ ወድቀዋል።

80 ተመልከቱ፡ በምድረ በዳ ላይ፡ "እኛ ብለዋል… " በፋሲካው ቀን፡ ከምንጩ በሚጠጣበት፡ ቅዱስ ዮሐንስ 6 ነው። ሁሉም ደስ አላቸው።

81 ኢየሱስ አለ፡ "በምድረ በዳ የነበረው ያ ዓለት እኔ ነኝ። ሰው ከእርሱ ዘንድ በልቶ የማይሞተው፤ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የወረደው እንጀራ እኔ ነኝ።"

82 እነርሱም አሉ፡ "አባቶቻችን በምድረ በዳ ለአርባ ዓመታት መና በሉ።"

እሱም "ሁሉም፡ አንድም ሳይቀር፡ ሞቱ" አላቸው።

83 **ሞቱ፡** ማለት ምን ማለት እንደሆነ፡ ቃሉ ወስዳችሁ መርምሩ፡ "ለዘላለም ተለዩ" ማለት ነው። ግን'ኮ፡ የአብራሃም ዘር ነበሩ። **ሞት** ማለት "መለየት፣ መጥፋት፣ ሙሉ በሙሉ መውደም፣ መጥፋት ነው።" የተገረዙ አይሁድ ሆነው ሳሉ፡ ኢየሱስ ሁሉንም፡ ሙታን አላቸው።

84 እያችሁ፡ ምስኪን ወዳጆቻችን፡ ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ፕሬስባይተርያን ነኝ፣ ትንሽ ተናዝዣለሁ፡ እንዲህ አርጌአለሁ፤ ይሄን ያህል'ማ ዲያብሎስም እንደኛ ያምናል።

85 በእርሱ ዘንድ መቆጠር አለባችሁ። እግዚአብሔርም በመንፈስ ቅዱስ ከማተም ጋር፡ መመስከር አለበት። በቃሉ ጥያቄ የለም!

86 "አይ፡ ያ'ኮ፡ ለሌላ ዘመን ነው፡" የምትሉ ከሆናችሁ፡ የሆነ ችግር አለ።

87 አንድ ሰው እየሮጠ ቢመጣ፡ ብርሃን መብራቱን ስትነግሩት፡ ወደ ምድር ቤት ታች እየሮጠ ወርዶ፡ እንዲህ ቢል፦ "እኔ ይሄን አልቀበልም። እኔ አልቀበልም። ብርሃን የሚባል ነገር የለም። እኔ አላምንም"? በዚያ ሰው ላይ የሆነ ችግር ሳይኖር አይቀርም። አእምሮው የታወከበት ሳይሆን አይቀርም። ሞቃታማ ጨረሩ እና ሕይወት-ሰጭ ምንጭ አልፈልግም ካለ፡ አእምሯዊ፡ ችግር አለበት።

88 እና አንድ ሰው፡ የእግዚአብሔርን ቃል በፊቱ ሲታወቅ እያየ፡ ሲበራ እያየ፡ የሃይማኖት ተቋም መጋረጃዎቹ አውርዶ ቢዘጋ፡ በዚያ ሰው ላይ፡ መንፈሳዊ ችግር አለ። የሆነ ችግር ይኖርበታል። መንፈሳዊ ስህተት አለበት። በቃ ሊቀበል አይችልም። "ታውረዋል፡ መታወሩም አያውቀውም" ፈራጁ እግዚአብሔር ሆኖ፡ ወደ ፍርድ ይሄዳሉ።

89 ልብ በሉ ይህን ሲ—ሲያደርጉ፡ እነዚያ ያመኑትን ዘሮች፡ ምን እንደሆኑ ተመልከቱ። የአብርሃምን ዘር፡ እስቲ አሁን አንዳንዶቹን እንፈትሻቸው።

90 የእብራውያኑ ልጆች እንውሰድ፡ ለእውነት ስለቆሙ የምስልን-አምልኮ መታገስን አልቻሉም። የአገሪቱ ንጉሥ ለሠራው ምስል ለመስገድ እምቢ አሉ። የተሠራው የቅዱሱ ሰው፡ የዳንኤል፡ አምሳል ነው።

91 የቅዱሳን ሰው ምስል በማምለክ የአሕዛብ ዘር በሐሰተኛው ወገን እንዲገባ መደረጉን ያሳያል። ሰዎች የሰዎችን ምስል እንዲያመልኩ በሚገደዱበት ጊዜ፡

አንድ አይነት አካሄድ ይኖሮዋል። በመገለጥ ገባ፡ በግንቡ ላይ በእጅ ጽሑፍ የተጻፈውን፡ ዳንኤል ቃሉን መተርጎም ቻለ። የገባበት መንገድ ይህ ነው፡ የሚወጣውም በዚሁ መንገድ ነው፡ በአሕዛብ ምስል፡ በተመሳሳይ መንገድ።

92 ልብ በሉ፡ አንሰግድም ብለዋል። ምን አደረጉ? ለቃሉ የታመኑ የአብርሃም ዘር ስለነበሩ፡ በእሳት መካከል፡ የጠላትን ደጅ ወረሱ። ተሳካላቸው። መቼም፡ የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው።

93 ዳንኤል፡ እውነተኛውን አንዱ አምላክ ሰለ ማምለኩ ተፈተነ። በዚህም ተፈተነ። በፈተናው ጊዜ ግን፡ በፈተናው ጸና። እንደ አባባላችን፡ ገንዘብ የወረደለት ከመሰለ በኋላ፡ እግዚአብሔር ምን አደረገ? እነርሱ የሚያደርጉትን ነገር አላወቁትም። ተበልቶ ይሞት ዘንድ ለአንበሶች ሊሰጡት ነበርና። ዳንኤል ግን እውነተኛ የሆነ አንድ አምላክ እንዳለ፡ በፈተናው ጸንቶ፡ የጠላቱን ደጅ ወረሰ። እግዚአብሔርም የአንበሳውን አፍ ዘጋለት።

94 በሐሰተኛ አሰመሳዮች፡ ኢያምብሬስና ኢያኔስ ፊት፡ ሙሴም በፈተናው፡ ስለ ተሰፋው ቃል ጸንቷል። ተመልከቱ፡ እግዚአብሔር፡ አሰቀድሞ በመለኮታዊ ኃይል ተገናኘው፡ እንዲህ አድርግ፡ ምልክቶችን አሳይ ብሎ ላከው፡ እያንዳንዷ ምልክት ድምጽ ነበራትና። ሙሴም እንደሚያውቅ ሆኖ፡ ወደዚያ ወረደ። ዱላውን በወረወራት ጊዜ፡ እባብ ሆና ተቀየረች። ምን እንደ ሆነ ታውቃላችሁ? አሰመሳዮች መጡና ተመሳሳይ ነገር አደረጉ።

95 ሙሴ፡ እጆቹን ጥሎ "ወይኔ፡ በቃ ይህ ሁሉ ስሕተት ነበር፡" አላለም። ባለበት ጸና እግዚአብሔርን ጠበቀ። ታምኖ ጠበቀ። ምንም ያህል አሰመሳዮች ቢኖሩም፡ ታምኖ ጸና። ህዝቡን ከዚያ ለማምጣት፡ ለጥሪው ታምኖ በጸና ጊዜ፡ የውሃው መዝጊያ በፊቱ በተጋረጠበት ጊዜ፤ እግዚአብሔር እንዲወርሰ አደረገው፡ በሚመራው በእሳቱ ዓምድ ደጁን ከፈተለት። ሕዝቡንም ወደ ተሰፋው ምድር ወሰዳቸው።

96 ሌላ ታላቅ መሪ፡ ኢያሱ ነው። ከነዚህ ሁሉ... ኢያሱ እና ካሌብ ብቻ፡ ወደ ተሰፋይቱ ምድር ገቡ። በዚያን ጊዜ የዓለም ማእከል ወደ ነበረችው፡ ቃዴስ ወደ ተባለ ሰፍራ መጡ፤ በዚህ ሁሉ የፍርድ ወንበር ያ ነበርና። እናም፡ ኦህ፡ አሥራ ሁለት ሰላዮች ምድሪቱ እንዲሰልሉ ተላኩ፡ አሥራ ሁለቱም ተመለሱ።

97 አሰሩ እንዲህ አሉ፤ "ኦህ፡ በጣም ብዙ ድካም አለው። እኛ አንችልም። እንግዲህ፡ በነዚያ ሰዎች፡ በፊታቸው እንደ አንበጣ ነን።"

98 ኢያሱ ምን አደረገ? ህዝቡን አረጋጋቸው። ሲናገርም "ሰሙኝ አንዴ። እኛ'ኮ ምንም ያህል ብናንሰም፡ ምንም ያህል ጥቂት ብንሆን፡ ማሸነፍ እንችላለን፡" አላቸው። ምን እያደረገ ነበር? "ምድሪቱን ሰጥቼሃለሁ፤" ለእያንዳንዷን ሰንዝር ግን ትፋለማለህ ላለው ተሰፋ ቃል፡ ጸንቶ ቆመ።

99 ይህን ታምኛለሽ፤ እናት? እግዚአብሔር ፈውስሽን ሰጥቶሻል፣ ለእያንዳንዷ ሰንዝር ግን ትፋለሚያለሽ። "እግራችሁ የረገጠው ሁሉ፡ ርስት አድርጌ ሰጥቻቿለሁ።" **ኮቴዎቻችሁ** ማለት "ርሰት።" ሁሉ የእናንተ ነው፡ እያንዳንዱ ተሰፋ የእናንተ ነው፡ ነገር ግን የሚጋፈጣችሁን ሰንዝር ሁሉ ትፋለማላችሁ።

100 አሁን፡ ኢያሱ እግዚአብሔር የተናገረውን ያውቃል። የአብርሃም ዘር ነዋ። አያችሁ? "እግዚአብሔር፡ ምድሪቱን እንደሰጠን እምናለሁ፡ ከማሸነፍም በላይ እንችላለን፡" አላቸው። በፈተናው ላይ፡ ከእስራኤል ወገን ሁሉ በተቃራኒ ጸንቷልና፤ ሕዝቡ ሁሉ በየነገዱ አዝነው አለቀሱ። ኢያሱ ግን "አይዟችሁ በርቱ! እግዚአብሔር ተስፋውን ሰጥቶናል፡" አላቸው።

101 ምንም ያህል አቅም ቢኖርህ፡ ተቃውሞው ምንም ቢሆን፡ ሐኪሙም ምንም ቢል፡ ተስፋን የሰጠ እግዚአብሔር ነው። ይሄን ማድረግ የእግዚአብሔር ነው።

102 ምን አደረገ? ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በወረደ ጊዜ፡ ደጁን ወረሰ። እሱ ያደረገው—ይህ ነው።

103 ኢያሪኮ፡ እንደ ኤሊ በቅርፊት ተዘግታ ነበር። ምን አደረገ? ደጇን ወረሰ።

104 አንድ ቀን ጠላቱ ሊያመልት ሲሞክር እንኳን፡ ፀሐይ እንድትቆም እስኪያዝዝ ድረስ የጠላቱን ደጅ እጅግ ወረሰ። ፀሐይም ታዘዘችለትና፡ ለሃያ አራት-ሰዓታት በጭራሽ አልዞረችም።

105 እንደምንም ይሁን፡ እግዚአብሔር ለገባው ኪዳን እውነተኛ ነው፤ ቃሉ ከሚወድቅ ሰማያትን ሁሉ ባዶ ቢያደርግ ይሻለዋል። ሊጠብቀው የማይቻለውን ቃል ኪዳን በጭራሽ አይገባም። "ደዌሽን ሁሉ የምፈውስ ጌታ እኔ ነኝ። በታመሙ ላይ እጃቸውን ቢጭኑ ይፈወሳሉ።" አሜን። "ሁሉም ነገር እንደሚቻል፡ ማመን ካቃተህ።"

106 ምድር እንዳትዞር ያደረጋት እግዚአብሔር ቢሆንም፡ ኢያሱ ግን አምኗል። ኢያሱ በጠላት ላይ እስኪበቀል ድረስ፡ ለሃያ-አራት ሰዓታት እንዳትዞር፡ ምድርን በሆነ ኃይል፡ በራሱ ኃይል ያዛት። ደጆቹን ወረሰ። አዎን፡ በትክክል ወርሷል። እግዚአብሔር ሁሌ እውነተኛ ነው።

107 ብዙ ጀግኖችን ለማየት ጊዜ ቢኖረን አሁን ደስ ይለኛ ነበር፡ ይሁን እንጂ አሥር ደቂቃ ብቻ ቀርቶኛል። ተመልከቱ፡ እነዚህ ድንቅ ጀግኖች ሁሉ፡ ታላላቅ የእምነት ተዋጊዎች፡ ሁሉም በሞት ደጅ ላይ ሞቱ። በሞት ደጅ ላይ፡ ሁሉም ጠፉ።

108 ከዚያ በኋላ የአብርሃም የንጉስ ዘር ብቅ አለ። ከይስሐቅ ጀምሮ፡ ሁሉም ፍጥራታዊ ዘር ነበሩ። አሁን ግን፡ የአብርሃም የእምነት ንጉሳዊ ዘር፡ ክርስቶስ መጣ፤ መሆን የሚገባን፡ መሆናችንን እና አለመሆናችን ብቻ ተመልከቱ። ፍጥረታዊው ዘር ጥላ ብቻ ነው። ሌሎች ሁሉ በፍጥረታዊው ልደት ተወለዱ፡ እርሱ ግን በድንግልና ልደት የመጣ ነው። አያችሁ፡ እሱ ከአብርሃም ዘር አይደለም፡ ወይም፡ አይሁዳዊ አይደለም። እርሱ የመጣው ከተስፋው ቃል በእምነት ዘር በኩል ነው። ስለዚህ፡ እኛም፡ በዚህ ሰው በኩል፡ ልጆቹ ልንሆን ይገባናል።

109 ያደረገውን ተመልከቱ። ይህ ንጉሳዊ ዘር፤ ምድር ላይ በነበረ ጊዜ፡ የጠላትን ደጆች ሁሉ አሸንፎ ወረሰ። በቃሉ ቃል ኪዳን ገብቶ። ድል ነስቷል። ስለ እኛ፡ የበሽታን ደጅ አሸንፏል። የመጣውም ለዚህ ነው። የታመማችሁ ሰዎች፡ የህመምን ደጅ አሸንፏል፡ ይህን አስታውሱ። እሱ ራሱ ድል ስለነሳ፡ ማሸነፍ አይጠበቅባችሁም። ሰዎች የራሳቸውን ደጅ ድል መንሳት ይኖርባቸዋል። እናንተ ግን ድል ነስቷልና፤ ድል መንሳት አያስፈልጋችሁም። የሕመምን ደጆችን ድል

አድርጓል። የሕመም ደጆችን ድል ሲያደርግ ምን አደረገ? እንዲህ ይሆናል እያለ... በምድር የምትለምኑት ሁሉ በምድርም የምታስሩት ሁሉ፡ በሰማይ አስረዋለሁ ብሎ፡ የደጁን መክፈቻ ሰጠን።

110 የፈተናውን ደጅ፡ በቃሉ ድል ነሳ። መክፈቻዎቹ፦ "ጠላትን ተቃወሙት፡ ከእናንተም ይሸሻል።" ሁሉን ድልነስቷል፡ ሁሉንም ዓይነት በሽታ ድል ነስቷል።

111 ሞትን ድል ነስቷል፣ ገሃነምንም ድል ነስቷል። ሞትን እና ሲኦልን ድል ነስቷል። ሌሎች ፍጥረታዊው ዘር ከመሆናቸው የተነሣ ያልቻሉትን፡ እሱ ድል አድርጓል። መንፈሳዊው ዘር ይህ ነው። የመቃብርን ደጅ ድል ነስቶ፡ በሦስተኛው ቀን፡ ስለ ጽድቃችን ተነሣ።

112 "አሁን ከአሸናፊዎች ሁሉ በላይ እንበልጣለን።" ልክ እንደ ርስት ወደ ውስጡ እንገባለን፤ "ከአሸናፊዎች በላይ።" አሁን የምንገጥመው የተሸነፈ ጠላት ጋር ነው። ህመም ተሸንፏል። ሞት ተሸንፏል። ሲኦል ተሸንፏል። ሁሉም የተሸነፈ ነው። ኦ፡ ማይ! መጠኔ ሁለት እጥፍ ብሆን ተመኘሁ፡ ምናልባት አሁን እጥፍ የሆንኩ ያህል ይሰማኛል። ከተሸነፈ ጠላት ጋር እየተጨቃጨቅን'ኮ ነው።

113 የጳውሎስ ጭንቅላት፡ ለመቁረጥ ግንብ በሠሩ ጊዜ፡ እንዲህ መናገሩ፡ አይደንቅም፡ "ሞት ሆይ፣ መውጊያህ የት አለ? እኔን ዋይታ እና አልቃሻ ልታደርጉኝ የምትችሉበትን ነገር አሳዩኝ። ሲኦል ሆይ፡ ድል መንሳትህ የት አለ፡ ደግሞም በዚህ እንድትቀርጹኝ ታስባላችሁ? እዚያ ወዳለው ባዶ ልጠቁማችሁ፡ እኔ ግን በእርሱ ውስጥ ነኝ በመጨረሻው ቀን ያስነሳኛል።" የተሸነፈ ጠላት!

114 የአብርሃም ንጉሳዊ ዘር! አሁን፡ ፍጥረታዊው ዘር ጣቱን አይቀሰርበትም። ንጉሳዊ ዘር ግን ድል መንሳትን ይቻለዋል፡ ከፊት ፊታችን እየቀደመ፡ ደጆቹን ሁሉ ድል ነስቶልናልና። እሱ አሁን፡ ኃያሉ ድል ነሺ፡ ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ፡ በመካከላችን አለ። ድል ያደረገው በሽታን ብቻ አይደለም... በሽታን ድል ነሳ። ፈተናን አሸነፈ። እያንዳንዱን ጠላት ድል አደረገ። ሞትን ድል አደረገ። ገሃነምን ድል አደረገ። መቃብርን ድል ነሥቷል፡ እንደገና ተነስቷል። ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላም፣ እነሆ ዛሬ ከሰዓት በኋላ፣ ኃያል ድል አድራጊ መሆኑን እያሳየ፡ በመካከላችን ቆሟል! አሜን። አሁንም ህያው ሆኖ፡ ተስፋ ቃሉን እያረጋገጠ፡ እዚህ አለ፡ የአብርሃም የዘውድ ዘር! ኦህ፡ ማይ! የጠላትንም...

115 "የጠላቱን ደጆች ድል ይነሳል።" ለእነኚያ፣ ዘር ለሆኑ፣ እራሱን ለማን ለመግለጥ ነው የቆመው? ሊያዩት ለሚቻላቸው አስቀድመው ለተወሰኑት ዘሮች። ያንን ድል ነስቷል። እነዚህም፡ ከቃሉ የተሰፋ ፈተና በኋላ፡ በመንፈስ ቅዱስ ማሕተም የታተሙትን፡ ወደ ክርስቶስ አካል ለታተሙት፡ ምን (ያረጋግጥላቸዋል? ) ዕብራውያን 13:8 እንዲሆን። አብራሃም ከሩቅ ባየው በእምነትም ባመነው፡ በመንፈስ ቅዱስ... በመንፈስ ቅዱስ ታትመዋል። እኛ ደግሞ የተናገረውን የተሰፋውን ቃል፡ ወደ ኋላ መለስ ብለን እያየን አሁን ተቀብለነዋል። ዮሐንስ 14:12 በዚህ በመጨረሻው ቀን፡ ድል በማድረግ በተነሳው በራሱ፡ ተረጋግጧል።

116 የሆነ ሰርዓት አይደለም፡ ነገር ግን ድል አድራጊ የሆነው፡ ያ ሰው፡ ክርስቶስ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ፡ በቤተ ክርስቲያኔ አይደለም፡ ባፕቲስት ቤተክርስቲያናችን አይደለም፡ ወይም የእናንተ ፕሬስቢስተርያን፡ በሜቶዲስት፡

ወይም በጴንጤዎች፡ በነዚህ አይደለም። እሱ ዛሬም ህያው ነው። ስለ ጽድቃችንም፡ በዚያ ላይ ተነስቷል።

117 እሱ ራሱ ህያው ስለሆነ፡ እናንተም ህያዋን ናችሁ ብሎናል። “በእያንዳንዱ ቃል እንጂ፡ ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም፡” በከፊል ቃል አይደለም፡ “ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ።” “እኔ ትንሳኤ እና ህይወት ነኝ። በእኔ የሚያምን፡ ቢሞትም እንኳ፡ ሕያው ይሆናል። በእኔ የሚያምን ሕያው ሁሉ ለዘላለም አይሞትም። ይህን ታምናላችሁ? ” የጠላት ደጅ ሁሉ ድል አድርጉ!

118 እግዚአብሔር ሳለ... ቦስዎርዝን እንዴት ያሸንፈዋል፡ ቦሰወርዝ በድል ነሺው ውስጥ ነውና። “በሕይወቴ ሁሉ በጣም ደስተኛ ሰዓቴ ይህች ናት።” ብሎ የተናገረበት ምክንያት ይህ ነው፡ ኧህ-ሀ። ኃያሉን ድል ነሺ አውቆታል። ዋስትናው በእርሱ ላይ አደረገ። ኦህ፤ ማይ! አሁን መዘመር እንችላለን፡

ህያው ሆኖ፡ ወደደኝ፡ ሞቶም፡ አዳነኝ፤
ተቀብሮ፡ ሐጢአቴን አራቀ፤
ተነስቶም፡ ለዘላለም በነጻነት ጸደቀ፤
አንድ ቀን ይመጣል፡ ኦ——ያቺ ድንቅ ቀን!

119 የተሸነፉ ለሚመስላቸው። ኤዲ ፔሮኔት፡ ይመስለኛል፡ ክርስትያን ዝማሬዎቹን መሸጥ አልቻለም። መዝሙሮቹን የሚፈልግ አልነበረም። ከዚህ ጋር ምንም ጉዳይ የለውም። ኦህ፡ አማኝ ሆኖ፤ የተሸነፈ ነበር! አንድ ቀን ግን መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይ ወረደ። ጽሑፎቹን የማይቀበል፡ የጠላቱን ደጅ ሁሉ! መንፈሱ ነካውና፡ ብዕሩን አነሳና፡ እግዚአብሔር የምረቃውን መዝሙር እንዲጽፍ አሰደረገው።

ሁሉም የኢየሱስን ኃያል ስም ያወድሱ!
መላእክትም ይሰግዱ፤
የንጉስ ዘውድም ያምጡ፤
የሁሉም ጌታ ያንግሱ።

120 ዕውሯ ፋኒ ክሮስቢ፡ አንድ ግዜ፡ እንዲህ አለች፦ “ዋት ዳዝ ኢት ሚን ቱ ዩ? ” አንዳንድ... እንደ ጴንጤው ኤሊቪስ ፕሪሌይ ቡኩርናዋን አልሸጠችም፡ ተሰጦአቸውን ለአለም እንደሸጡት፡ እንደነ የቸርች-ኦፍ-ክራይስቱ ቦኔ፡ እና ሬድ ፎሌ እንዳደረጉት፤ የመርከብ ካዲላኮች፡ እና ሚሊዮን-ዶላር፡ የወርቅ ክምችቶች አላቸው። ፋኒ ክሮዝቢ ግን ለጥሪዋ ታማኝ ሆነች። እንዲህም ብላ ዘመረች፦

አዳኝ ሆይ፤ አትለፍብኝ፤
ጸሎቴን ስማኝ፤
ሌሎችን አንተ ስትጠራ፤
አትለፍብኝ።

አንተ የመጽናናቴ ሁሉ ምንጭ፤
ከሕይወት በላይ ለእኔ፤
በመሬትስ ከአንተ ሌላ ማን አለኝ?
ወይስ በሰማይ አንተ እንጂ?

121 “ወደ ገነት በሄድሽ ግዜ ዕውር ብትሆኚስ? ” አሏትና፡

“ምንም ቢሆን፡ እሱን አውቀዋለሁ፡” አለች።

“እንዴት ታውቂዋለሽ? ” አሏት።

“ያኔ አውቀዋለሁ።” አለቻቸው።

“ወይዘሮ ክርዝቢ፡ ሚልዮን ዶላሮችን እኮ ማፈስ ትችያለሽ።” አሏት።

“ሚልዮን ዶላሮችን አልሻም፡” አለቻቸው።

122 “ሃው ዊል ዩ ኖው ሂም? ” አለች፤

አውቀዋለሁ፡ አውቀዋለሁ፤
ይቤዠኛል በጎኑም ያቆመኛል፤
አውቀዋለሁ፡ አውቀዋለሁ።

123 “እሱን ማየት ባልችልም፡ የእጆቹ የሚስማር ጠባሳዎችን እዳብሳለሁ” በማለት የጠላቷን ደጅ ድል ነሳች። አዎን።

124 በክርስቶስ ከሆናችሁ! አላቸው፡- “በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፤ የምትፈልጉትን ቁልፍ ጠይቁ፡ የትኛውን ድጅ መውረስ እንደምትፈልጉ ጠይቁ፡ መሻትህን ለምን፡ ለአንተም ይሰጣል። በእኔ ብትኖሩ፣ እና ቃሌ በእናንተ ውስጥ ቢኖር፣ ከፊትህ የሚመጣውን ማንኛውንም የጠላት ደጅ ድል መንሳት ይቻላል።” እናንተ የአብርሃም የንጉስ ዘር ናችሁ።

125 ምን ዓይነት ደጅ በፊታችሁ ይቆማል? ህመም ከሆነ፡ ለህመምም ከአሸናፊዎች በላይ ናችሁ። እንግዲያውስ ይህ ጥሩ የጥንት መዝሙር እንዘምር፡ ማለት እንችላለን፡-

በመጽሐፉ ውስጥ ያለው ተስፋ ሁሉ የእኔ ነው፡
እያንዳንዱ ምዕራፍ፣ ቁጥር ሁሉ… መለኮት ሁሉ፡
በመለኮታዊ ፍቅሩ እታመናለሁ፡
የመጽሐፉ ተስፋ ሁሉ የእኔ ነውና።

126 ከአሸናፊዎች በላይ ነን፤ የአብርሃምም ዘር የጠላትን ደጅ ይወርሳል! እነዚህ ነገሮች ሊሆኑ አይችሉም ሲሉ፡ ዲያብሎስ፡ ብኤልዜቡል፡ ወይም ሌላ ነገር ብለው ለመጥራት ሲፈልጉ፡ እግዚአብሔር ግን ደጆችን ሁሉ ድል ነሰቶ ጠላትን እንደሚያንበረክክ እርግጥ ነው።

እንጸልይ።

127 ጌታ ሆይ፡ የአብርሃምን ዘር የሆኑት ሁሉ… እንደሚያዩት አውቃለሁ፡ ጌታ ሆይ። ቃሉ እውነተኛ ማሳ ካላገኘ በቀር እንዴት ሊወርድ ይቻለዋል? ያሰተውሉት ዘንድ እጸልያለሁ። ወደ ጸሎቱ ሰልፍ የሚመጣ ሰው ሁሉ የተፈወሰ ይሁን።

128 ጌታ ሆይ፡ ገና ንስሀ ያልገቡ፡ በሰው ፊት መጽናት ያልቻሉ፤ እንዲሁም ለክርስቶስ ያልቆሙ፡ ተራ እና ቀዝቃዛ የሆነውን፡ የሃይማኖት ሰርዓት ሁሉ፡ እና ከአንተ ያራቃቸው የሞተ ነገር ሁሉ ለመካድ የተዘጋጁ፡ አንዳንዶች እዚህ ቢኖሩ። አሁን ይነሱና፡ “እንደ አዳኜ እቀበልሃለሁ” ይበሉ። አንተም በዚያ ሰለነሱ ትቆማለህ።

129 እራሶቻችን ዝቅ እንዳደረግን፡ እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ቁሙና፡ እንዲህ በሉ፡ “በመለኮታዊ ህልውና፡ በዚያ ቀን ለእኔ

እንዲቆምልኝ አሁን ለእርሱ መቆም እፈልጋለሁ።" ለመቆም ከፈቀዳችሁ፡ ስሞቻችሁ በህይወት መዝገብ ላይ እንዲጻፍ እድል እሰጣችኋለሁ፤ እጠይቃችኋለሁ። የቱንም ቤተ ክርስቲያን እንድትቀላቀሉ አልጠይቃችሁም። እዚህ ሆናችሁ፡ ክርስቶስን የማታውቁ ካላችሁ፡ ወደሱ ቅረቡ እላችኋለሁ።

130 ጌታ ይባርክህ፡ ልጄ። "እኔ—ልቆምለት እፈልጋለሁ።" የሚል ሌላ ሰው አለ፡ ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት። ጌታ ይባርክሽ፡ እህቴ። "እፈልጋለሁ... " ጌታ ይባርኮት። ጌታ ይባርኮት። "በዚህ ከከሰዓት፡ አቋሜን እወስዳለሁ።" እነዚህ መልካም ሰዎች፡ ወንዶችና ሴቶች፡ ቆመው፡ "ዛሬ ከሰዓት፡ የራሴን አቋም እወስዳለሁ።"

131 በዚያ ቀን ሐኪሙ፡ "እንግዲህ፡ ሰባራው፡ ደሙ እየፈሰሰ ነው፡ ሞት በላዩ፡ ወይም በላይዋ ነው ሲል።" ወይም፡ አንድ ቀን ማለዳ፡ አቋምህ ትዝ ይልሃል። አሁን ቁምለት።

132 "በሰው ፊት በኔ የምታፍር ከሆነ፡ በአባቴ እና በቅዱሳን መላእክት ፊት ስለ አንተ አፍራለሁ። በሰው ፊት ብትመሰክርልኝ ግን፡ እኔ በአባቴና፡ በቅዱሳን መላእክቱ ፊት እመሰክርለታለሁ።"

133 እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ። በረንዳው ውስጥ ሌሎች ይኖሩ ይሆን? አሁን፡ እነሱን እየጠበቅን። አንዳንዶቹ፡ ብዙ በዋናው ምድር ቤት ላይ? መልካም። እንደ ቃልህ ተቀብየሃለሁ፡ ወዳጄ።

134 በውሃው ጉድጓድ እንደነበረች ሴት፡ ቃሉ መልካም መሬት ላይ ከወደቀ፡ እሷ—እሷ ተረድታለች። እሷ በመሰረቱም፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት-... በመንግሥተ ሰማይም ተወክላለች። ብርሃን ሲያንጸባርቅበት፡ ያኔ አውቀዋለች።

135 እግዚአብሔር ይባርክህ ወንድሜ። እንዲህ ነው ጀግንነት... እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። በሕይወታችሁ ታላላቅ ነገሮችን አድርጋችሁ ይሆናል፡ አሁን ግን፡ ለክርስቶስ መቆማችሁ፡ በዘመናችሁ ካደረጋችኋቸው ታላላቅ ነገሮች ሁሉ የላቀ ነገር ማድረጋችሁ ነው።

136 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ በዛሬው ከሰዓት በኋላ፡ ዘሩ በተወሰነ መሬት ላይ ወድቋል። ሕይወት ሲበቅልም እያየን ነው። ወንዶችና ሴቶች በእግራቸው ቆመዋል፡ ሁሉን-የሚያይ የእግዚአብሔር ዓይን፣ በሁሉ የሚገኝ፣ ሁሉን የሚያውቅ፣ ሁሉን ቻይ የሆነውን አይቷቸዋል። አባት ሆይ፡ የአንተ ናቸውና። እንደ ምርኮ፡ ወዳንተ አቀርባቸዋለው።

137 ያደረጉትን አውቀው፡ አሁን የቆሙለትን ምን ማለት እንደሆነ አውቀው፡ ይህን ልምምድ፡ አቋማቸውን ስለ ክርስቶስ ከተናቁት ከታናሹ ወገን ጋር ማጽናት ይሁንላቸው። ፊትህ እስከሚቆሙባት ቀን ድረስ ታምነው የጸኑ ይሁኑ፡ ከዚያም ያ ተወዳጅ ድምፅ፡ "አዎን፣ አባት ሆይ፡ በባቶን ሩዥ፡ እና ዴናም ስፕሪንግስ በሚባል ትንሽ ቦታ ላይ ስለ'ኔ ቆሟልና፡ አሁን በተራዬ ስለ'ሱ፡ ስለ'ሷ እቆማለሁ" ይበልላቸው። ጌታ ሆይ፡ የአንተው ናቸውና አድርግላቸው። በኢየሱስ ስም። አሜን።

እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ የቆማችሁ። እግዚአብሔር መቼም...

138 አሁን አንድ ነገር አርጉልኝ። ፓስተሮች ባሉበት ዙርያ ከሆናችሁ፡ ፈልጋችሁ፡ ጥቂት አነጋግሩዋቸው፡ እያችሁ። በክርስቲያን ጥምቀት፡ ካልተጠመቃችሁ፡

ተጠመቁ። አሁን ከአማኞች ጋር ሁኑ፡ ከእውነተኛ ጋር፡ ከአስመሳይ-አማኝ ጋር አይደለም፡ ከእውነተኛ አማኞች ጋር።

አሁንም እንጸልይ፡ ለእነዚህ መሃረቦች ደግሞ እንጸልይ።

139 የሰማይ አባት ሆይ፡ እነዚህ መሃረቦች አሁን ይወጣሉ፡ ወዴት፡ አላውቅም። ምናልባት ለአንድ ሽማግሌ ዓይነ ሰውር አባት አንድ ረግረጋማ በሆነ ሰፍራ ውስጥ ተቀምጦ፡ መሃረቡ እስኪደርስለት ለሚጠባበቅ፡ ሆስፒታል አልጋ ላይ ለተኛ ህጻን ልጅ፡ እናቱም፡ በጉጉት ቆማ፡ የነዚህን መሃረቦች መምጣት ለምትጠባበቅ። የሰማይ አባት ሆይ፤ አብረህ ትሄድላቸው ዘንድ እጸልያለሁ። ስለዚህ ቃልህ እንደሰበክነው፡ በአንተ ስላለን እምነትና የዛሬ ህልውናህ ምልክት እንዲሆን፡ በአብራሃም ዘንድ የነበረች እምነት እና፡ በኢየሱስ ክርስቶስ አፍርታ ለእኛ የተሰጠች እምነት፡ ከእነዚህ ጋር ትሂድና መሃረቦቹን የነካ ሰው ሁሉ ትፈውስ። በኢየሱስ ስም፡ ላክነው። አሜን።

140 አሁን የፀሎት ሰልፍ ከመጥራታችን በፊት፡ ለአፍታ ብቻ። ሁሉን ቻዩና ኃያል አምላክ፡ ታላቅ የሆነው፡ ለሁሉም-የሚበቃው... እባካችሁ፡ ወዳጆች፤ አሁን ለ—ለታመሙት መጸለይ እጀምራለሁ፡ እና... ምናልባት፡ ሰትወርዱ፡ አንዳንዶች ከጊዜው በፊት መሄድ ከፈለጋችሁ፡ የ—የምናገራችሁ ላይኖረኝ ይችላልና መሄድ ትችላላችሁ። ምንም ሁን ማን፡ ቀደም ሲል፡ ያልቆማችሁ፡ እርግጠኛም ካልሆንክ...

141 የቤተክርስቲያን አባል ከሆናችሁ፡ ጥሩ ነገር ነው፡ በቂ ግን አይደለም። አያችሁ፡ ወጣቱ ባለጸጋ የቤተክርስቲያኒቱ አባል ነበር። አያችሁ? የዘላለም ሕይወት ለማግኘት ምን ማድረግ እንደሚገባው ኢየሱስን ጠየቀ። በጭራሽ አልተቀበለም። ረግጦ ወጣ። ወጣቱ ይህን ማድረጉ ሞኝነት ነበር። እንደሱ አትሁኑ። ቀድሞ የሚታወቅበትን ታስታውሳላችሁ? ትንሽ ቆይቶ፡ በለፀገ። ሀብታም ሆነ። ጎተራዎቹ እንኳን እስኪፈሱ ድረስ። ብኋላ ፋጻሜውን ስንመረምር ግን፡ በእሳት እየተሰቃየ፡ አድራሻው በገሃነም ሆነ። ይህ እንዲደርስባችሁ አትፍቀዱ። አትፍቀዱለት፡ ክርስቶስን ተቀበሉ።

142 እናንት ወጣቶች፣ ወጣት ሴቶች፣ ወጣት ወንዶች፣ በዚህ በህይወት ሽግግር ላይ፡ እባካችሁ ይህን አታድርጉ። እንደምወዳችሁ፡ እንደ—እንደ ወንድማችሁ፡ እኔን ሰሙኝ። እዚህ ያለሁት ስለምወዳችሁ ነው። ጌታን እወዳለሁ፡ እናንተንም እወዳችኋለሁ፡ እናንተን ሳልወድ ጌታን ልወድድ አልችልም።

143 ማስተላለፍ የምትፈልጉት አስተያየት ካለ፡ በልጄ ወይም እዚህ ባሉት በልጆቼ በአንዱ፡ ብታስተላልፉት፡ እጅግ እመርጣለሁ። እስኪ ደግሞ... እኔ፡ ልለፈው። የትኛውም ወላጅ ያደርገዋል፡ እግዚአብሔርም ጭምር። አያችሁ? ህዝቡን ይወዳል። እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ።

144 “ለምን ትገስጻቸዋለህ? ” ትላላችሁ፡ እውነተኛ ፍቅር ይገራል።

145 ልጃችሁ በጎዳናው ላይ ቢቀመጥ፡ “አይ፡ ሳቢሳዬ እዚያ ተቀምጧል። እንዲህ’ማ ማድረግ የለበትም፡ ትንሽ ግን ስሜቱን መጉዳት አልፈልግም፡” ትላላችሁ። ስለዚህ አትወዱትም። እዚያው ሊገድሉት ነውና። ከወደዳችሁት፡ ታመጡትና አስገብታችሁ ትንሽ ግርፋት ይሰጠዋል። እንዲታዘዝ ታደርጉታላችሁ።

146 እግዚአብሔር የሚሰራበት መንገድ እንዲሁ ነው። ፍቅር ይገራልና፡ እውነተኛ ፍቅርም ይሄው ነው።

147 ሴቶች ፀጉራችሁን ስትቆራርጡ፡ ቀለምና ሌላ ነገሮች እየተቀባችሁ፡ ስባኪ ሲቆም የማይገራችሁ ከሆነ፡ እውነተኛ ፍቅር በዚያ የለም፡ ትዝም አይላቸውም። ወንዶችንም ሶስት አራት ጊዜ አጋብተው ወዘተ፡ በዚያው ቢያስቀጥሏችሁ፡ እውነተኛ ፍቅር በዚያ የለም። ወደ ቤተክርስቲያን እንድትቀላቀሉ፡ ጀርባችሁ መታ መታ አድርገው፡ በሐይማኖት ስርዓት ያፍኗችኋል፡ እንዲህ በማለት፡ "ማድረግ ያለብሽ፡ ቅድስት ቤተክርስትያን መቀላቀል ነው፡" በዚያ ፍቅር የለም። ወይም፡ ወይም ደግሞ፡ ሰውየው፡ ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል፡ ታውሯል።

148 እውነተኛ ፍቅር እርማት አለው፡ ወደ እግዚአብሔር ቃል ይመልሳችኋል።

149 ኢየሱስን ተመልከቱ፡ እንዴት፡ እና ምን እንዳለ፡ ስለእነርሱ እስኪሞት ድረስ፡ ስለወደዳቸው፡ ስለ ደሙ እንኳን ሲጠሩ።

150 አሁን ታላቁ መንፈስ ቅዱስ... እስኪ ለአፍታ ያህል ቆየት ላርገው። ከመጀመራችን በፊት፡ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት በላዬ ላይ እስኪመጣ ድረስ ልጠብቀው። እየሰበክኩ ስለነበር። ስለ ትብብራችሁ፡ አመስግናለሁ።

151 አሁን፡ እዚህ ያላችሁ ሁላችሁ፡ የትም ብትሆኑ፡ በሕንፃው በየትኛውም ቦታ ያላችሁ፡ ለአንድ ደቂቃ ያህል፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ እርዳኝ! እርዳኝ! ልብስህን ልንካ፡" ብላችሁ ጸልዩ። ይሄውላችሁ፡ ሴቲቱ ልብሱን በነካችው ጊዜ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ በአካል አልተሰማውም፡ ዘወር ብሎ ግን ማን እንደሆነች እና ምን እንዳደረገች አወቀ። ዛሬም ከሰዓት በኋላ ያው ኢየሱስ፣ በድካማችን ስሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህን ነው።

152 አሁ፡ ሁላችሁ፡ ቃል ኪዳን የገባልን አምላክ፡ እውነት መሆኑን፡ እና ዳግም (እንደው ይግለጥልን) በሰዶም ዘመን እየኖርን እንዳለን ታምናላችሁ? ስንቶች ታምናላችሁ፡ በህንፃው ውስጥ ያላችሁ፡ እጃችሁን ብቻ አንሱ።

153 በሰዶም እንደነበረ፡ እንዲሁ፡ እየኖርን ነው። የዓለም ስርዓት፣ ሁሉም፣ የቤተክርስቲያን ስርዓት፣ የፖለቲካ ስርዓት፣ ስርዓቱ ሁሉ ተበርዟል። የቀረ የለም። ፖለቲካው እጅግ ቆሽሿል። በየስርዓቱ፣ በሁሉም ስፍራ፡ አምባገነኖቻችን፡ እንዳለ ቆሽሿል። ቤተክርስቲያንም ያው ሆናለች። ቤተሰብ ያው ሆነዋል። በቃ ቆሽሿል፡ ሰዶም!

154 እግዚአብሔር፡ ይሄን ከእናንተ በፊት እንደሚያውቀው፡ አስታውሱ፡ በሰው ሥጋ ምሳሌ ተገልጦ ከሰዶም በፊት እንዳደረገ፡ የተሰፋው ቃል ልጅ ከመምጣቱ በፊት፡ ያደረግኩትን ደግሜ አደርጋለሁ እንዳለ አስታውሱ። መጀመርያ እንዳደረገው፡ የተሰፋውን ቃል ልጅ የሚያስተዋውቅ ሰው እንደሚልክ፡ ቃል ገብቷል፤ ደግሞም፡- "የሰው ልጅ በሚገለጥበት ጊዜ፡" ብሏል።

155 እኔና አንቺ አንተዋወቅም። እሺ፡ ወይዘሮ ቶምፕሰን፡ የሴት እና ተዛማጅ ችግሮችሽ፡ እግዚአብሔር እንደሚፈውስሽ ታምኚአለሽ? ወይዘሪት፣ ወይዘሪት ቶማስ፡ ታምኚዋለሽ? ፈቃደኛ ነሽ? ያድነኛል ብለሽ ታምኚአለሽ? እንግዲያውስ፡ እጆችን ወደ ላይ አንሺ።

156 ከኋላሽ የተቀመጠች እመቤት። እየጸለየች ናት። የአርትራይተስ በሽታ አለባት።

157 ከአጠገቧ የተቀመጠ አንድ ሰው፡ የሆድ ችግር አለበት፡ እየጸለየ ነው። ሊያልፋችሁ ነው፡ አይናችሁን አትግለጡ። ከዚህ አይደላችሁም። ከወደ ሚሲሲፒ ናችሁ። አቶ እና ወይዘሮ ስትሪነር ናችሁ። በፍጹም ልብ ካመናችሁ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውሳቿል። ማመን ከቻላችሁ። ታምናላችሁ? እንግዲያውስ ተቀበሉ። እሺ። እናንተ መሆናችሁ ህዝቡ ያይ ዘንድ እጃችሁ ወደላይ አንሱ።

158 ሰዎቹን አላውቃቸውም። በሕይወቴ፡ ጭራሽ አይቼአቸው አላውቅም። ወዳጄ፡ ማመን አለብህ። እሱ እራሱ አድራሻውን እያሳየ ነው። በሙሉ ልባችሁ፡ ታምናላችሁ?

159 ራስህን ለምን ነቀነቅክ፡ አለቃ፡ ለምንስ እንዲህ አይነት አስተያየት አየኽኝ? የስ፡ ሰር። ይሄን በማድረግህ፡ ለአፍታ ከአንተ ጋር እነጋገራለሁ። ተቀምጠህ እያየኽኝ ያለኸው፡ ጨዋ ሽማግሌ። ቅንነት በተሞላበት፡ አስተያየት አየኝ። አምኗል። ስትሮክ ላጋጠመው ሰው እየጸለይክ ነው። የጸሎትህ ዋናው ነገር—ግን፡ አንተ የምትፈልገው፡ እየፈለግክ ያለኸው የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀትን ነው። ትክክል ነው። ኧህ-ሃህ። ልክ ነው። እመቤት፡ ካመንሽ! ሥራ እየፈለግሽ ነሽ። በተጨማሪም፤፡የእግዚአብሔር ነቢይ፡ እና አገልጋይ እንደሆንኩ ታውቂ ዘንድ፡ ሁለት ቀዶ ጥገናዎችን ተደርጎልሻል። እጅግ ደካማ አድርጎሻል። በሁሉም ዓይነት ሁኔታዎች፡ መንፈሳዊ ችግር። ሁሉም እንደተስተካከለ ልነግርሽ እፈልጋለሁ። እምነትሽ አድኖሻል።

160 [ባዶ ቦታ በቴፕ ላይ—አርታዒ።]... እዚያው ከጎንሽ የተቀመጠች። ጸሎት ላይ ናት። ወደዚህ ተመልከቺ። ሰምቶሻል፡ አንቺም ነክተሽዋል። እኔ አላውቅሽም፡ እሱ ግን ያውቅሻል። ስትጸልይበት የቆየሽውን ጉዳይ ልንገርሽ። በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽ? የፊኛ ችግር አጋጥሞሻል፡ እየጸለይሽ ነው። እግዚአብሄር እንደሚፈውስሽ ደህና እንደሚያደርግሽ ታምኚያለሽ? ወይዘሮ ሰሚዝ ነሽ። ልክ ነው። እጅሽን አንሺ።

161 አያችሁ፡ እራሱን እያስተዋወቀ ነው። ምንድነው? የአብርሃም ዘር ነው፡ ለአብርሃም የነበረለት እምነት፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ መካከል፡ ምልክቶች በማስከተል፡ ቃሉን የሚያረጋግጥ።

162 የሚጸለይላቸው ካርዶች ስንት ናቸው፡ እነማን ናቸው እጃቻችሁን ከፍ አድርጉ፡ ካርድ አግታቿል? ኦህ፡ የፀሎት ሰልፍ ብንጀምር ይሻላል።

163 አያችሁ፡ ገብቷቿል አይደል? አሁን መንፈሱ ይህን ብቻ... አይፈውስም ብቻ አይደለም። እሱ እዚህ መገኘቱ ብቻ ነው የሚያስረዳው። ፓስተሮቻችሁም ለታመሙት መጸለይ ስልጣን አላቸው። ፈውስ ግን አይፈውሱም፡ በጭራሽ፡ በእርግጠኝነት አይፈውሱም። ያው ስልጣን ግን—አላቸው፡- "ምልክቶቹም አማኞችን ይከተላሉ።"

164 አሁን ፓስተሮች ጓደኞቼ ወደዚህ እፈልጋችኋለሁ። (መልካም ነው፡ ከጉባኤው ይጠሩ... ? ... )

165 በሙሉ ልባችሁ የምታምኑ ስንት ፓስተሮች፣ አገልጋዮች እዚህ አላችሁ፣ የምታምኑ? ኦህ፡ አመሰግናለሁ። ትቆማላችሁ ብዬ አሰባለሁ? ወደዚህ ኑ፡ አንድ ደቂቃ ከእኔ ጋር ቁሙ፣ እዛ ጋር፡ ለታመሙት ጸልዩላቸው። ኑ ወደታች ውረዱ። ምን እንደሚከሰት ታያላችሁ፡ አሁን ፈውሱ ሲከናወን ታያላችሁ።

166 እንድትመጡ እፈልጋለሁ፡ እ—እዚህ ጋር ድርብ መሰመር አድርጉ። ለታመሙ ለመጸለይ ወደዚያ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ወደዚያ እመጣለሁ። ራሳቸውን እንደ አማኝ ለመቆጠር የሚፈልጉ አማኝ ፓስተሮችን እፈልጋለሁ፡ እዚህ ስትመጡ፡ ቅዱስ ህይወት፡ ንጹህ ህይወት እንደምትኖሩ፡ የምታምኑ። አስታውሱ፡ የክርስቶስን ወንጌል በመወከል፡ ምን እየመጣ እንዳለ ወዲህ እዩ!

167 ወንድም ብሌር፡ እዚያ እንዳለህ አውቃለሁ፡ ወይም ወንድም ፓት። ሁሌም እንደምታደርጉት ያንን ድርብ መሰመር እስኪ ሰሩት፣ ከፈቀዳችሁ፣ አንተና ወንድም ፓት።

168 እምነት ያላቸው የሚያምኑ ፓስተሮች! እንግዲህ፡ ተመልከቱ፡ እግዚአብሔር በቃሉ፡ እራሱን ከቃሉ ጋር ከተቆጠረ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ፡ ኢየሱስ የተናገረውን የምታውቁ፡ "ያመኑት እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል። እጃቸውን በታመሙ ላይ ቢጭኑ፡ ይድናሉ"? ፓስተሮች፡ እራሳችሁን እንደ አማኝ ለመቆጠር ቀርባችኋል። አይደል? አማኞች ናችሁ (አይደላችሁም እንዴ?)፡ እዚህ መቆም ባልቻላችሁ ነበር። ኢየሱስ ምን አለ? "ያመኑት እነዚህ ምልክቶች ይከተላቿል።" እኔም ከእናንተ ጋር አብሬ አማኝ ነኝ።

169 ወደታች እመጣለሁ። ይህ ህዝባችን ነው እኛም በመንጋው ላይ እረኞች ነን። አሁን መረቤን ከእናንተ ጋር ለመዘርጋት እወርዳለሁ፡ እጆቼን ከእናንተ እጆች ጋር ለማኖር። ሰዎቹ ሲመጡ፡ በአእምሮአችሁ ውስጥ ትንሽ ጥርጣሪ ወይም ማንኛውንም ነገር ካለ፡ አሁኑኑ አሰወግዱ፡ ሰዎቹ በሚያልፉበት ጊዜ፡ እያንዳንዳቸው ሲያልፉ፡ እኛም እጃችን በጫንባቸው ግዜ፡ ይፈወሳሉ። አሁን ሁላችሁ፡ በሙሉ ልባችሁ ታምናላችሁ?

170 ሌሎች ሲያልፉ የምትጸልዩ ሰንቶች አላችሁ እዚህ፡ "ልጸልይ ነው።" እጃችሁ ወደላይ አንሱ፡

171 አስታውሱ፡ አባታችሁ፣ እናታችሁ፣ ሴት እና ወንድ ልጃችሁ፣ እህት ወይም ወንድም ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ሰልፍ ላይ የሚመጡት፡ ዘመዳችሁ ባይሆኑም፡ የሌላ ሰው ዘምድ ናቸው። ዘመድ ቢሆን ኖሮስ፡ በካንሰር፡ ወይም በሌላ አስከፊ በሽታ ቢታመም፡ ከልባችሁ አትሆኑም ነበር ሰዎች? በትክክል፡ እንሆን ነበር።

172 አሁን፡ እኔ አምናለሁ፡ የምታደርጉት... አሁን **በዚህ** ረድፍ ላይ ያላችሁ፡ እነዚህ መተላለፊያዎች፡ ከጸሎት ካርዱ ጋር፡ **በዚያ** ወገን በኩል ቁሙ። በቀኝ በኩል ያላችሁ ሁሉ፡ ከዚያ ጎን በኩል ቁሙ። አሁን፡ የግራውን ክፍል ያዙ፡ እያችሁ፡ መንገዱ፡ ሁላችንም እንዳለ ተጨናንቋል፡ እናንተም እንዴት፡ ምን እንደምንሰራ አታውቁም። መልካም፡ **በዚህ በኩል** ያላችሁ ሁሉ፡ **እዚህ** ጋር ቁሙ። አሁን፡ በቀኝ-በኩል ያላችሁ ሁሉ፡ እናንተ ሄያጆች ስለሆናችሁ፡ ወዲህ ኑ፡ ኑ ወደዚህ።

173 እና አወጣጣቸው፡ እንዴት ይውጡ፡ ወንድም ቦርደርስ? በቀጥታ በጎን በኩል ባለው በር፡ ወድያውም ዞራችሁ ወደ ህንፃው ውስጥ ትመለሳላችሁ።

174 ስለዚህ፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ **ይህ** ወገን በሚጠራበት ጊዜ፡ እነሱ ይነሳሉ። እና አሁን ምን እንደ ሆነ እንመልከት... መልካም፡ **በዚህ** በኩል ያላችሁ፡ በዚያች በኩል ትመለሳላችሁ። የፀሎት ካርዳችሁን ይዛችሁ፡ በዚህ በኩል እለፉ። እናንተም በበረንዳው ውስጥ ያላችሁ፡ እነሱን ለመገናኘት ወደ መጨረሻው ሰልፉ ታች ውረዱ። በዚህ በግራ-እጅ በኩል ያላችሁ፡ ወደ

ግራው-ጥግ ሂዱ። አያችሁ፡ ከዛ በኋላ፡ እናንተም ከሰልፋችሁ **በዚያ** መንገድ ተመልሳችሁ፡ ተመለሱሰና፡ **በዚያ** በኩል ዙሩ። አያችሁ? እና ሰልፋችሁን በትክክል ትከታተላላችሁ፡ ከዚያ በኋላ በጭራሽ ምንም መደበላለቅ አይኖርም።

175 እና ከዚያ በበረንዳው ውስጥ ያላችሁ ቦታችሁን መተላለፊያ ላይ ብቻ አስተካክላችሁ፡ ሲያልፉም እንደመጡ ወዲያው መውጣት።

176 አሁን፡ አሁን **እዚህ** አከባቢ ጀርባ ላይ ይሄን መሰመር እስክታገኙት ድረስ፡ እያንዳንዱ፡ አሁን ከኋላ መራመድ ይጀምር። ወደዚህ አካባቢ ኑና፡ እዚህ ጋር፡ ልክ **እዚህ** እየተንቀሳቀሳችሁ **ወደዚህ** መሰመር ዙርያ መምጣት ጀምሩ።

177 ኦህ፡ አሁን ምን ሊሆን ይችላል! ምን ሊሆን ይችላል! ይህ ጊዜ አንድ ነገር የግድ መከሰት ያለበት ጊዜ ሊሆን ነው። መልካም።

178 አሁን፡ ልክ እንደሱ፡ **በዚያ** ዙርያ ወደኋላ ሂዱ፡ እናም ወደ ሰልፉ ተቀላቀሉ፡ እንደሱ። በዚህ መተላለፊያ መንገድ ላይ ሂዱ። እንዲሁ ነው አደራረጉ አሁን።

179 እንዲሁም፡ እያንዳንዳችሁ በእግሮቻችሁ እንደቆማችሁ፡ አሁን ጸሎት ማድረግ እንጀምራለን። እናም እንድትፈወሱ፡ ይህ ጉባኤ ከእኔ ጋር ይጸልያል። አሁን እምነት ብቻ ይኑራችሁ። እንዲሁም አት...

180 በዙሪያው ኑ፡ ወደዛ ወደ ኋላ፡ ወደዚህ አከባቢ ቀረብ ቀረብ በሉና ከኋላ ወዳለው መሰመር ተቀላቀሉ። ኑ ወደዚህ፡ አንድ ትልቅ መሰመር ሰሩ። **እንደሱ** እያላችሁ ቅረቡና፡ እንዲቷን መሰመር ሰሯት። ይሄው ነው።

181 ሁሉም በጸሎት ውስጥ ይሁን። አሁን በእውነተኛ እምነት ውስጥ ሁኑ። በቃ አሁን ህዝቡ ላይ አትኩሮት አታድርጉ። እኛ—ሁላችንም በኢየሱስ ክርሰቶስ መገኘት መከበባችን፡ አስታውሱ፡ በቃሉ በማመን፡ በመካከላችን ያደረገውን እንድናከብር እኛ ላይ የተመሰረተ ነው።

182 ጥሩ ነው። አሁን በቃ ጥሩ እየሆነ ነው። ያ መሰመር ልክ በሚያስደንቅ ሁኔታ እየገባ ይመስለኛል።

183 አሁን ሁሉንም እንደቆሙ፡ በህንጻው ውስጥ፡ ያለ ሰው ሁሉ፡ እራሱን ዝቅ እንዲያደርግ እፈልጋለሁ።

184 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ሊሆን ተቃርቧል። ውሳኔው አሁን መደረግ አለበት። አሁን እዚህ ሰለመሆንህ ይኖረን ይሆን? እንወድሃለን ወይ? ጌታ ሆይ፡ ሰለምንጠይቅህ ነገርስ፡ በቂ እምነት አለን ወይ? ይህ ህዝብ በሰልፉ በመቆም አድራሻቸውን እየለዩ ናቸውና። ጌታ ሆይ፤ በከንቱ አይሁን። እንዲህ ይሁን፡ ጌታ ሆይ፡ እያንዳንዳቸው በዚህ ያልፋሉና፡ ከክርሰቶስ ሰር ሆነው ሲያልፉ እንደነበሩ፡ እሱ እዚህ እንዳለ አውቀነዋልና። ፈውሳቸው ይቀበሉም ዘንድ እንጸልያለን። በሚቀጥሉት ሳምንቶች እና ሳምንቶች ውስጥ እንኳን፡ እነዚህ ሰዎች ወደ ፓስተሮቻቸው እንደሚሄዱ እርግጠኛ ነኝ፡ የሴቶች ችግር ያጋጠማቸው ሴቶች፡ የሆድ ችግር፡ ፕሮሰቴት ያላቸው ወንዶች፡ ሁሉም ዓይነት ችግሮች፡ ይፈወሳሉ፡ በህልውናህ ናቸውና፦ "እንዴ፡ ህመሙ አሁን ተወኝ እኮ፡" ይበሉ። አሁን መጥተው ይ—ይህን የሞትክለትን አላማ ይቅዱት። የአብርሃም ዘር ናቸውና፡ አንተም ሰለ እነሱ ድል ነሰተሀልና። የሰጠሃቸውን መጥተው ይቀበሉ።

185 አንተ ሰይጣን፡ የተሸነፍክ ፍጡር መሆንህን እስክታውቅ ድረስ፡ በዚህ ሳምንት፡ በጣም ተጋልጠሃል። ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አሸንፎሃል። በሦስተኛው ቀን፡ ለጽድቃችን ተነስቶ፡ አሁን በመካከላችን ቆሟል። እምነታችንም እሱን ይጠባበቃል፡ ከአንተ እና ከሰራኸው ማንኛውም ነገር ርቀናል። ልቀቅ እነዚህን ሰዎች፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም።

186 [ባዶ ቦታ በቴፕ ላይ—አርታዒ።]... ? ... መምህሩ እንድናደርግ እንዳዘዘን አድርገናል። በዚያ መስመር ውስጥ ያለፋችሁ፡ ሰንቶቻችሁ ደህና እንደምትሆኑ ታምናላችሁ፡ እጃችሁን ወደላይ አንሱ። እኔም ከእናንተ ጋር አነሳለሁ።

187 እንደ አገልጋዮች ቡድን፡ በመጨረሻ፡ እዚያ ጋር ያደረግነው ነገር፡ አብዛኞቹ ታመው ነበር፤ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ ጉባኤዎቻቸው ወደ ውስጥ ለማስገባት የተቻላቸውን እየሞከሩ ነበር፤ ይግቡም አይግቡም። እውነተኛ እረኞች እንዲህ ናቸው። መንፈስ ቅዱስም፦ “እያንዳንዱ እጅ ለእጅ እንዲያያዙ አድርጋቸው ብሎኛል።” ልባችንን እና መረቦቻችንን፡ እና ጸሎቶቻችንን፡ አንድ ላይ አደረግን።

188 ኢየሱስ ሆይ፡ እነሱን አድናቸው። እናም በጌታ ቃል ጠንካራ፡ ጠንካራ እረኞች አድርጋቸው።

189 ወንድሞቼ፡ እግዚአብሔር፡ የልባችሁን ምኞቶች ሁሉ ይስጣችሁ። ሁል ጊዜ እሱን ማገልገል ይሁንላችሁ፡ ይህንን መልካም ህዝብ ለማገልገል፡ በሕይወታችሁ ውስጥ የእግዚአብሔር ኃይል ይሁንላችሁ። ከእኛ ጋር የነበረው ሁል ጊዜም ከእናንተ ጋር ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እርሱ ራሱ ከዚህ በፊት ካደረገው በበለጠ በእናንተ ዘንድ ጉልህ ይሁንላችሁ።

190 እናንት ሰዎች፡ አንዳች የአካል ጉዳተኞች የነበራችሁ፡ ለተወሰነ ጊዜ ምንም ልዩነት ላታዩ ትችላላችሁ፡ ምንም ልዩነት ላይታይ ይችላል። አብርሃም ያደረገውን ተመልከቱ። የምትፈልጉት ይህ አይደለም፡ ለውጥም አይኖረውም። የህመማችሁ ምልክቶቻችሁን አትመልከቱ። የተናገረውን ተመልከቱ። “አሁንም ህመሙ ይሰማኛል፤” ብትሉ፤ ከሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። እግዚአብሔር አድርግ ያለውን ፈጽማቿዋል። አያችሁ፡ ያንን አትመልከቱ። የተናገረው ነገር ተመልከቱ፡ እግዚአብሔርም ሆነ አለ! አምናለሁ። እናንተስ አታምኑም? በሙሉ ልቤ፤ አምናለሁ።

191 ዳግመኛ እስከማያችሁ ድረስ ጌታ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ጸሎቴ ለእናንተ፡ ሌሊቱም እጅግ አይጨልምባችሁ፡ ዝናቡ በኃይል አይክበድባችሁ። እጸልይላቿለሁ። ጸልዩልኝ። ዳግም እስክንገናኝ፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። አሁን ወደ ወንድማችን ወደ ፓስተሩ፡ እሺ።

**ከፈተና በኋላ የጠላትን ደጅ መውረስ** AMH64-0322

(Possessing The Gate Of The Enemy After Trial)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ በመጋቢት 22፡ 1964፡ እሁድ ከሰዓት ላይ፡ በዴንሃም ሰፕሪንግ ሃይ ሰኩል ዴንሃም ሰፕሪንግሰ፡ ልዊሰያና፡ ዩ.ኤሰ.ኤ.፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org